# ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ

...ዕለታዊ የመንፈሳዊ ጥናት መጽሃፍ

*Chris Oyakhilome*

LoveWorld Publishing

Unless otherwise indicated, all Scripture quotations are taken from the *King James Version* of the Bible.

A KEY FOR OTHER BIBLE VERSIONS USED:

NKJV -New King James Version
AMP -The Amplified Bible
AMPC -The Amplified Classic Bible
TANT -The Amplified New Translation
TLB -The Living Bible
CEV -Contemporary English Version
NASB -New American Standard Bible
ISV -International Standard Version
NIV -New International Version
MSG -The Message Translation
WEB -The World English Bible
TNLT -The New Living Translation
ASV -American Standard Version
TEV -Today's English Version
RSV -Revised Standard Version
GNB -Good News Bible
WNT -Weymouth New Testament
NRSV -New Revised Standard Version
MOFFAT -Moffatt New Translation
WESNT -Wesley New Testament
EBR -Rotherham's Emphasized Bible
DRB -Douay-Rheims Bible
TPT -The Passion Translation
CJB -Complete Jewish Bible

ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ...ዕለታዊ የመንፈሳዊ ጥናት መጽሃፍ

ISSN 1596-6984

ይካቲት 2013 edition

Copyright © 2013 by LoveWorld Publishing

FOR MORE INFORMATION AND TO PLACE ORDERS:

**UNITED KINGDOM:**
Unit C2, Thames View Business Centre, Barlow Way Rainham-Essex, RM13 8BT.
Tel.: +44 (0)1708 556 604
+44 (0)08001310604

**USA:**
Christ Embassy Houston,
8623 Hemlock Hill Drive
Houston, Texas. 77083
Tel.: +1(800) 620-8522

**NIGERIA:**
Plot 97, Durumi District, Abuja, Nigeria.

Plot 22/23 Billingsway Road, Oregun, Ikeja, Lagos.
P.O. Box 13563 Ikeja, Lagos
Tel.: +234 1 8888186

**SOUTH AFRICA:**
303 Pretoria Avenue
Cnr. Harley and Braam Fischer,
Randburg, Gauteng 2194
South Africa.
Tel.:+27 11 326 0971

**CANADA:**
LoveWorld Publishing Canada
4101 Steeles Ave W, Suite 204
Toronto, Ontario
Canada M3N 1V7
Tel.:+1 416-667-9191

***www.rhapsodyofrealities.org***
***email: rorcustomercare@loveworld360.com***

All rights reserved under International Copyright Law. Contents and/or cover may not be reproduced in whole or in part in any form without the express written permission of LoveWorld Publishing.

# መግቢያ

የ2013 ዓ.ም. ተወዳጁ “የራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ “እትም፣ የመንፈሳዊ ህይወትህ እርምጃና እድገት ለማሳደግ በተለየና ባማረ ሁኔታ ለተሻለ ነገር በሚያነሳሳ መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመረጃና በመገለጥ ከተሞሉ ፁሁፎች በተጨማሪ የዚህ ወር ዕትም በየዕለቱ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ መገኘት ለማወቅ በምታደርገው ጉዞ እምነትህን በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንድታሳድግ በተመቻቸ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ቀርቦልቃል፡፡ በየቀኑ ባጠናኸው፣ ባሰላሰልከውና በአፍህ በተናገርከው ወይም ደግሞ ባወጅከው መጠን እየታደስክ ትሄዳለህ፡፡

## - ይህንን መነቃቅያ እንዴት በበለጠ መጠቀም ይቻላል -

- ይህን ጽሁፍ አንብብና በጥንቃቄ አሰላስል፡፡ ፀሎቶቹንና የአፍ ምስክርነት ቃሉን በየቀኑ ለራስህ ድምጽህን ጎላ አድርገህ መናገርህ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወትህ እንዲያልፍ ያደርጋል፡፡
- የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም በአዲሱ የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት  በሚገባ አንብቡ
- የዕለታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ ንባቡን በጠዋትና በማታ ከፍለህ ማንበብ ትችላለህ
- መነቃቅያውን  በጸሎት ተጠቀሙበትና በእያንዳንዱ ወራት ያላችሁን ግብ ጻፉና ከአንዱ ግብ ወደ ሌላው ግብ ያላችሁን ስኬት በሚገባ ለኩ

የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ በወሰድን ጊዜ የእግዚአብሔርን የክብር መገኘትና ድል ዓመቱን በሙሉ እንዲደሰቱበት ጥሪ እናደርጋለን፡፡ በጣም እንወዳችኋለን፡፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

-ፓስተር ክሪስና አያኪሎሜ

# የግል መረጃ

ስም

አድራሻ

ስልክ

# ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ

...ዕለታዊ የመንፈሳዊ ጥናት መጽሃፍ

WWW.RHAPSODYOFREALITIES.ORG



ሰኞ 1

# የሚያስፈልጋችሁ ለእናንተ የሰጣችሁ ቃል ነው

ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው፥ ባሪያህም ወደደው (መዝሙር 119: 140)።

የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር የመፍጠሪያ መንገድ ነው። ኃይሉ ያልተገደበ ነው። ቃሉ ሁሉን ፈጠረ፣ ዛሬም እንደምንግዜውም ውጤታማ ነው። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እና በማንኛውም የሕይወታችሁ ወቅት፣ የሚያስፈልጋችሁ እርሱ የሰጣሁ ቃል ነው።

ንጉሥ ሰለሞን ያደረገውን ነገር አስቡ፤ እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ፣ እርሱን እጅግ የበለጠ ጥበበኛ እንዴት አደረገው? በቃሉ ነበር! በሌሊት በሕልም ለሰለሞን ተገለጠለት እና “ምን ትፈልጋለህ?” ሲል ጠየቀው።

ሰለሞን ጥበብን እና ማስተዋልን ጠየቀ (1ኛ ነገሥት 3:8-9)። እግዚአብሔር ጥበብን ወደ ሰለሞን አዕምሮ ውስጥ ለማስገባት አንጎሉን “አልከፈተም”፤ ያለው ነገር “ሰለሞን ተቀብለሀል!” ነው። “እኔ እንደ ቃል አድርጌልሃለሁ እነሆ፥ ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተም በኋላ እንዳይነሣ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ ልቡና ሰጥቼሃለሁ” (1ኛ ነገሥት 3:12)። እግዚአብሔር ይባረክ!

ሰለሞን እነዚህን ቃላት በተቀበለት ቅጽበት ለእርሱ እና በእርሱ ውስጥ እግዚአብሔር እንደተናገረው ሆነ። ጥበብ እና አስተዋይ ልብ ለእርሱ ተካፈለ። ለአብርሃምም እንደዚሁ አደረገ፤ እንዲህ አለ “...ስምህ አብርሃም ይሆናል ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና” (ዘፍጥረት 17:5)።

ሚስቱ መካን ስለነበረች አብርሃም ልጅ አልነበረውም ነገር ግን እግዚአብሔር የብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁ አለው። “ስምህ አሁን አብርሃም ይሆናል ምክንያቱም ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና።”

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚታየው ነገር ምንም ቢሆን ግድ አይልም ነበር፤ የሸመገለ አካሉን ወይም ሙት የሆነውን የሳራን ማኅፀን መመልከትን እንቢ አለ፤ እግዚአብሔር የተናገረውን ብቻ ማወጅ ጀመረ።

ግድ የሚለው ለእናንተ የሰጣችሁ የእርሱ ቃል ነው፤ ድላችሁ ያ ነው። ሮሜ 4:19-21 ላይ ያለውን አንብቡ፤ እንዲህ ይላል፡- “መቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ...በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም” የሚሰራው እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር ሲናገር እና እርሱ ከተናገረው ጋር በመስማማት ስታውጁ፤ ለእናንተ የሆነው ቃል እውን ይሆናል፤ ቃሉ በሕይወታችሁ እና በሁኔታችሁ ሁሉ ያሸንፋል። ሃሌሉያ!

## የእምነት አዋጅ

በቃሉ አማካኝነት መንፈሴ በርቷል፤ የመንግስቱን ምስጥራት እና ኃይል መረዳት አለኝ። የሚለውን በእኔ ውስጥ እያፈራ፣ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወቴ ውስጥ ስላለ፣ እኔ አልሸነፍም፤ ዛሬ በሁኔታዎች እንድገዛ እና የበላይ እንድሆን በቃሉ በርትቻለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

መጽሀፈ ምሳሌ 4:10; መጽሀፈ ምሳሌ 4:20-22; ትንቢተ ኢሳያስ 55:10-11

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 22:15-46 & ኦሪት ዘጸአት 22-23

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 11:21-30 & ኦሪት ዘፍጥረት 32

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ማክሰኞ 2

# አስቀድሞ የእርሱ በረከቶች ሁሉ ተፈጽመዋል



> እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃሉ ሁሉ በእርሱ ተፈጽሟል፥ ስለዚህ ለእግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ክብር ስንሰጥ አሜን እንላላን
> (2ኛ ቆሮንቶስ 1:20)።

የእግዚአብሔር ቃል ለእናንተ ተራ የሆነ ተስፋ አይደለም፤ ቃሉ ተጨባጭ ስለሆነ እውነታ መገለጫ ነው። በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ለሆኑ ገና የሚፈጸሙ ተጨማሪ ተስፋዎች የሉም። ተስፋ ምንድን ነው? አንድ ሰው አንድ የተወሰነ ነገር እንደሚያደርግ የሚገልጽበት ነው። ይህ ቃል ለሚነገረው ሰው ድርጊቱ ይፈጸማል ብሎ እንዲጠብቅ ወይም ነገሩ እንዲፈጸም የመጠየቅ ወይም በትእግስት የመጠበቅ መብት ይሰጠዋል።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ገና ይፈውስሃልና እንዲፈውስህ መጸለይ አለብህ የሚል የለም፤ ምክንያቱም በክርስቶስ አስቀድሞ አድርጎታል! ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሁሉ ፍጻሜ ነው፡፡

የትኛውንም የተስፋ ቃል ፍጻሜ እየተጠባበቅን አይደለም። አሁን የእርሱ ቃል እውነት አለን እንዲሁም በቃሉ እውነት እንኖራለን። "አቤቱ ጌታ ሆይ ልትፈውሰኝ ቃል ገብተሃል" ወይም "ጌታ ሆይ ነጻ ልታወጣኝ ቃል ገብተኸልኛል" ማለት አያስፈልጋችሁም። እንዲህ መናገር ክርስቶስ ለማድረግ የመጣውን ነገር አለማወቅ ወይም ሙሉ በሙሉ አለመረዳት ነው። እርሱ የመጣው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ሁሉ ሊፈጽም ነው፤ እርሱ ለእናንተ የእግዚአብሔር በረከት ነው።

ለክርስቲያን ጥሩ ጤንነት የተስፋ ቃል አይደለም፤ ብልጽግና የተስፋ ተስፋ አይደለም፤ የኃጢአት ስርየት የተስፋ ቃል አይደለም፤ ነጻ መውጣት የተስፋ ቃል አይደለም፤ ቅድስና የተስፋ ቃል አይደለም፤ እንዲሁም ጽድቅ የተስፋ ቃል አይደለም። እነዚህ ሁሉ በክርስቶስ በነጻ የተሰጣችሁ የእግዚአብሔር በረከቶች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና

በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን...” (2ኛ ጴጥሮስ 1:3)። መታገልን አቁሙ። በክርስቶስ ያላችሁን ሕይወት አጣጥሙ።

## የእምነት አዋጅ

እኔ የእግዚአብሔር ወራሽና ከክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔር ወራሽ ነኝና የእግዚአብሔር የሆነው ሁሉ የእኔም ነው። የወንጌል በረከት ሙላት በክርስቶስ ለእኔ የሚቻል እና የሚገኝ ሆኖ ቀርቦልኛል፡፡ እግዚአብሔር በሰማያዊ ስፍራ ባለ በረከት ሁሉ ባርኮኛል፤ ብልጽግና፥ ድል፥ ስኬት፥ ሀሴት፥ ሰላም እና የመንግስቱ በረከቶች ሁሉ አሁን የእኔ ናቸው! እግዚአብሔር ይመስገን!

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ጴጥሮስ 1:3-4; 1 ቆሮንጦስ 3:21-22

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 23 & ኦሪት ዘጸአት 24-25

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 12:1-9 & ኦሪት ዘፍጥረት 33

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ረቡዕ 3

# በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መግዛት

> በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ (ሮሜ 5:17)።

የተሰመረበት "በ" የሚለው ቃል በግሪክ "ዲያ" የሚል ነው፤ ትርጉሙም "በኩል" ማለት ነው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት እንነግሣለን። በሺህ አመቱ መንግስት ጊዜ የምንነግሠው በእርሱ በኩል ሳይሆን ከእርሱ ጋር ነው። እንዲሁም በአዲሱ ሰማይና ምድር ከእርሱ ጋር እንነግሳለን። መጽሐፍ ቅዱስ "...ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ" ይላል (ራእይ 20:6)። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2:12 ላይም እንዲህ ይላል፡- "ብንጸና፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤ ብንክደው፥ እርሱ ደግሞ ይክደናል።" ግን ይህ ሁሉ የወደፊት ነው። አሁን ግን በዚህ ሕይወት በእርሱ በኩል እንነግሣለን። ሃሌሉያ!

በዚህ መረዳት ተመላለሱ። ቃሉ በሮሜ 6:4 ላይ የተናገረውን አስተውሉ፡- "እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።" ይህ አዲሱ ሕይወት የንጉስ ሕይወት ነው። ራእይ 5:10 እርሱ ንጉስ እና ካህናት አደረገን፥ በምድርም ላይ እንነግሣለን ብሏል።

በንጉስ እሴት እና አስተሳሰብ እናንተ አዲስ ሰው ናችሁ፤ ዓለምን በተለየ መንገድ፤ ከድል እና ከመግዛት እይታ ተመልከቱ። የመክፈቻ ጥቅሳችን በአምፓሊፋይድ መጽሀፍ ቅዱስ ትርጉም፣ በሕይወት ግዛት ውስጥ እንደ ንጉስ እንነግሣለን። እናንተ ንጉስ ናችሁ፤ እንደ ንጉስ ግዙ!

በቃል ግዙ፤ ንጉሦች የሚያደርጉት እንዲህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል "የንጉሥ ቃል ኃይለኛ ነውና ..." (መክብብ 8:4) ። በቃላችሁ አማካኝነት የበላይነትን ተለማመዱ። በሰይጣን እና በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ ትዕዛዝን አውጡ እናም እነርሱ ይሰሟችኋል እንዲሁም ይታዘዟችኋል፤

ምክንያቱም የምትመላለሱት በክርስቶስ ግዛት ውስጥ ነው።

ከክፍላችሁ ሆናችሁ የነገሮችን አካሄድ እና ሁኔታዎችን መቀየር ትችላላችሁ። በምንም ነገር በጭራሽ መረበሽ የሌለባችሁም ለዚህ ነው ። ሁኔታው ምንም ይሁን ምን እምነት በተሞላ ንግግራችሁ ነገሮች ከእግዚአብሔር ፍቃድ ጋር ተስማምተው እንዲሄዱ ማድረግ ትችላላችሁ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

## የእምነት አዋጅ

በዚህ ሕይወት በጽድቅ እንድነግስ ጸጋ ተሰጥቶኛል። ትዕዛዝን አወጣለሁ እርሱም ይጸናል፤ ምክንያቱም እኔ የምሰራው በክርስቶስ ውስጥ፥ ከክርስቶስ ጋር እና በእርሱ ስልጣን ነው። በሽታን፥ ውድቀትን፥ መሸነፍን እና ሞትን እቃወማለሁ። ከእግዚአብሔር ያልሆነን ነገር ሁሉ አልቀበልም እናም ከእርሱ ፍጹም ፍቃድ ጋር የሚስማማውን ብቻ እወስዳለሁ። ሃሌሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 5:17 AMPC; የዮሐንስ ራዕይ 5:9-10

| የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት |
|---|
| የማቴዎስ ወንጌል 24:1-35 & ኦሪት ዘጸአት 26-27 |

| የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት |
|---|
| የማቴዎስ ወንጌል 12:10-21 & ኦሪት ዘፍጥረት 34 |

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# መንፈስ ቅዱስ - የአብ በረከት

> እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው (ሐዋርያት ሥራ 5:32)።

ሉቃስ 11:13 መንፈስ ቅዱስን ስለመቀበል በብዙዎች ዘንድ የተሳሳተ አፈጻጸም እና የተሳሳተ መረዳት የሚታይበት ጥቅስ ነው። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ እንዲህ አለ "እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" ነገር ግን እየተናገረ የነበረው ስለ ክርስቲያኖች ሳይሆን በብሉይ ኪዳን ለነበሩት ነው።

ማንም ሰው መንፈስ ቅዱስን በመጠየቅ መቀበል ይችላል፤ ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙዎች አላገኙም ምክንያቱም ስላልጠየቁ ነው። ኢየሱስ ጠይቁ ይሰጣችኋል አለ (ሉቃስ 11:9) ። ነገር ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ የተነሳ አዲስ ኪዳን ከመጣ በኃላ፣ ቃሉ ለማንም መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይጠይቅ አላለም። የተነገረን እንዴት ሐዋሪያት መንፈስ ቅዱስን ለሌሎች ሲያገለግሉ እንደነበር ነው፤ እነርሱ "መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው" (ሐዋርያት ሥራ 8:15) ፤ እናም አንዳንዶች ያለጸሎት ተቀበሉ (ሐዋርያት ሥራ 10:44-46) ።

እግዚአብሔርን ለመንፈስ ቅዱስ መጠየቅ ትርጉም የለውም፤ መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች ሁሉ ከተሰጠው አስፈላጊ ከሆኑት የእግዚአብሔር ስጦታዎች ውስጥ አንዱ ነው። ወንጌልን በማመን እና የእርሱን ጥሪ በመታዘዝ ማንኛውም ሰው መንፈስ ቅዱስን ሊቀበል ይችላል። የሐዋሪያት ሥራ 2:17 ላይ እንዲህ አለ፡- "በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ..." የሐዋሪያት ሥራ 5:32ን፥ ዕብራውያን 5:9ን፥ ሮሜ 2:8ን ተመልከቱ።

የተናገረው "በሁሉም ክርስቲያኖች ላይ..." የሚል እንዳልሆነ ልብ በሉ። ይህ የአብ በረከት ነው። አሁን መጥቷል። ያለ መንፈስ ቅዱስ የክርስትናን ሕይወት መኖር አትችሉም። እግዚአብሔር በመንፈስ ሙላት

እንድትመላለሱ እና በዚህ ሕይወት በጽድቅና በድል እንድትኖሩ ይፈልጋል።

ዳግም ከተወለዳችሁ ጀምሮ እስካሁን መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበላችሁ ከሆነ፣ የመክፈቻ ጥቅሳችን እንዲህ ይላል (ገላትያ 3:14) ፡- “የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል...”። አሁን በቀላሉ እንዲህ በሉ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ልቤን እከፍታለሁ እናም መንፈስ ቅዱስን እቀበላለሁ”፤ ከዛም ክርስቶስን በእምነት እንደተቀበላችሁ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ። አሁን እያመሰገናችሁት በመንፈስ ተሞልታችሁና በልሳን ልትናገሩ ወይም ትንቢትን ልትናገሩ ትችላላችሁ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

## የእምነት አዋጅ

እኔ ልቀት እና ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነ ሕይወት እኖራለሁ፤ ምክንያቱም መንገዴን በሚመራኝ እና በድል፥ በክብር፥ በመግዛት እና በኃይል እርምጃዬን በሚያስተካክለው መንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ። ሕይወት ሰጪ እና የበረከት ምንጭ አድርጎኛልና እርሱ ዓለምን በእኔ ይባርካል። እግዚአብሔር ይባረክ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሐዋርያት ስራ 19:6-7; የዮሐንስ ወንጌል 6:63 AMPC; ትንቢተ አሞጽ 2:28-29

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 24:36-51 & ኦሪት ዘጸአት 28

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 12:22-30 & ኦሪት ዘፍጥረት 35

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



አርብ **5**

# ሕይወታችሁን በእውነት ላይ ገንቡ

> ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው
> (መዝሙር 119:105)።

ብዙዎች ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ቃል ከመመስረት ይልቅ በተሳሳተ መረጃ፣ ግምት እና በሰዎች ሀሳብ ላይ ይመሰርታሉ። ከዚህ ዓለም እና በውስጡ ካለው ነገር ሁሉ በተለየ በቃሉ ላይ መተማመን ትችላላችሁ፣ ቃሉ ፍጽም እና የማይለወጥ ነው፣ ቃሉ ዘላለማዊ ነው እናም ልትኖሩበት የሚገባ የመረጃ ምንጫችሁ መሆን አለበት።

ብዙዎች መረጃን ለማግኘት የሚሄዱበት በይነ-መረብ በተሳሳተ እና እውነተኛ ባልሆነ መረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላችሁን እምነት ሊያጠፋ ተበላሽቷል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢየሱስ፣ ነቢያት በተናገሩት ነገሮች ላይ በተቃርኖ ይጽፋሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚቃረኑ ነገሮችን ስላገኘን መሻሻል አለበት ይላሉ። እነዚህ መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው፣ የተሳሳተ አዕምሮ ያላቸው እና አታላዮች ናቸው!

መጽሐፍ ቅዱስ በምድር ላይ ብቸኛ እና እጅግ አስተማማኝ የሆነ መጽሐፍ ነው። በጌታ ፊት ስትቆሙ የታሪክ አስተማሪያችሁ ወይም መምህራችሁ ያስተማሯችሁን ነገር አይጠይቃችሁም። የሚጠይቃችሁ ስለ ቃሉ ነው፤ ምክንያቱም በቃሉ ውስጥ ያለው መረጃ በእግዚአብሔር ምሪት የተጻፈ ነው።

የመከፈቻ ጥቅሳችን በሕይወታችሁ ውስጥ የሚሰጠውን የምሪት አገልግሎት ያሳየናል። የምትሰሙት ወይም የምታነቡት ምንም ይሁን ምን፣ የቃሉን መመሪያ እና መንገድ ብቻ ተከተሉ። ሕይወታችሁን በእግዚአብሔር እውነት ላይ ገንቡ፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ ስለ ቃልህ ስጦታ አመሰግንሃለሁ። ዛሬ አስደናቂ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲመራኝ በማስገዛት፣ ልቤን እና አዕምሮዬን ለቃልህ እከፍታለሁ። ቃሉን በመንፈሳዊ መረዳት ሳጠና ለቤተክርስቲያን፣ ለእኔ እና ለዓለም ስለዓለፈው፣ ስለ አሁኑ እና ስለ ወደፊት ያለህን ዕቅድ እና ዓላማ ጥልቅ እይታን እቀበላላሁ። እናም ወደ ቀጣይ የስኬት፣ የድል እና የብልጽግና ደረጃ አድጋለሁ፣ እውነጨፋለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ጢሞቴዎስ 3:14-17; የዮሐንስ ወንጌል 14:26; የዮሐንስ ወንጌል 17:17

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ  ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 25:1-30 & ኦሪት ዘጸአት 29-30

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 12:31-38 & ኦሪት  ዘፍጥረት 36

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ቅዳሜ 6

# እጆቻችሁ የተባረኩ ናቸው

> ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም (1ኛ ቆሮንቶስ 6፡15)፡፡

ኢየሱስ በማርቆስ 16፡18 እንዲህ ብሏል፡- "እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ"፣ ምክንያቱም የእናንተ እጆች ተራ ሳይሆኑ የኢየሱስ እጆች ናቸው፡፡ በመግቢያ ጥቅሳችን ያነበብነው ይህንን ነው፡- "ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን?" እግሮቻችሁ የክርስቶስ ናቸው፣ አይኖቻችሁ የክርስቶስ ናቸው፡፡ እርሱ በእናንተ ይራመዳል፣ ይናገራል፣ ያያል፣ይባርካል፡፡ ሀሌሉያ!

አንዳንዴ ክርስቲያኖች "እጆቼ የተባረኩ ናቸው..." ሲሉ ስሰማ እደነቃለሁ፤ የሚናገሩትን ቢያስተውሉት የሚያውጁትን እውነት ሀይል ቢረዱት እላለሁ፡፡ እጆቻችሁ የተባረኩ የሆኑት የኢየሱስ ስለሆኑ ነው፤ እናም ለበረከት እንድትሆኑ አድርጓችኋል፡፡ ስለሆነም እጆቻችሁ የእናንተ (በረከት የሆናችሁ) ቅጥያዎች ናቸው፤ ምክንያቱም እናንተ የክርስቶስ ቅጥያዎች ናችሁ፡፡ ሀሌሉያ!

ስለዚህ እጆቻችሁን መጠቀም ተማሩ፡፡ በእጆቻችሁ የድል ሀይል አለ፡፡ እጆቻችሁን ለጸሎት እና ለአምልኮ ስትዘረጉ ወይም ስታነሱ የተትረፈረፈ መለኮታዊ ሀይል ይፈሳል፡፡ እንዲቀየር በምትፈልጉት ሁኔታ ላይ ወይም ጉዳይ ላይ ወይም የሆነ ሰው እንዲባረክ የምትፈልጉ ከሆነ እጆቻችሁን በምትዘረጉ ጊዜ የሚሆነው እንዲሁ ነው፡፡

ለምሳሌ በቤታችሁ የሆነ ችግር ካለ ወይም በህይዎታችሁ እንዲቀር የምትፈልጉት ሁኔታ ካለ በከንፈራችሁና በእጆቻችሁ የፈለጋችሁትን ነገር መቀየር ትችላላችሁ! መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋርያት ሥራ 5፡12 በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር ይላል፡፡

እጆቻችሁን ስትዘረጉ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ተስፋዎች ይታደሳሉ፣

ሸክሞች ይቀላሉ፣ ህመምና በሽታዎች ይፈወሳሉ፣ የህይዎት ፍጻሜዎች ያምራሉ፡፡ በእምነት እጆቻችሁን ተጠቀሙ፣ ተአምራትም ሲደረጉ ተመልከቱ፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በእኔ ውስጥ ስላለው ሀይልህ አመሰግንሀለሁ፡፡ ለፈውስ፣ ነጻ ለማውጣት፣ሸክምን ለማቅለልና ሰዎች እንዲበለጽጉ ለማድረግ መለኮታዊ ችሎታ በእኔ ውስጥ አስቀምጠሀል፡፡ለአለሜ የመፍትሄ ጥቅል ነኝ፡፡ ሌሎችን ለመባረክና ከፍ ለማድረግ በእኔ ስለሚሰራው ጸጋህ አመሰግናለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ኦሪት ዘጸአት 17:11-13; የሉቃስ ወንጌል 4:40-41; የማርቆስ ወንጌል 16:17-18

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 25:31-46 & ኦሪት ዘጸአት 31

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 12:39-50 & ኦሪት ዘፍጥረት 37

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



እሁድ 7

# ክብሩን በውስጣችሁ ተሸክማችኋል

> እግዚአብሔር ጽዮንን ይሠራታልና፣በክብሩም ይገለጣልና፡ ፡ይህ ለሚመጣ ትውልድ ይጻፋል...
> (መዝሙረ ዳዊት 102፡16፣18)፡፡

በምድር ላይ አንድ ክርስቲያን ሊቀበለው የሚቀረው አንድ ነገር ብቻ አለ፤ ይህም የቁሳዊ አካሉ መክበር ወይም መለወጥ ነው፡፡ ይህም ማለት ከሰማይ የሚመጣ አዲስ ቁሳዊ አካል እንለብሳለን፡፡ ይህም መቼ እንደሚሆን መጽሀፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡52-52 እንዲህ ያስተምረናል፡- "በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፣ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይገባዋልና"፡፡

አሁን የክርስቶስን ክብር በምድራዊ ማደሪያችን ተሸክመናል፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡7 ጳውሎስ መዝገብ ይለዋል፤ "ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጅ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን"፡፡ የእግዚአብሔር ብርሀን በመንፈሳችሁ ውስጥ አለ፡፡ የክርስቶስን ፍጽምና ተሸክማችኋል፡፡ሀሌሉያ!

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ፡-በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና" (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡6) እናንተ የእግዚአብሔር ማደሪያ ናችሁ! ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ህያው ነው፡፡ ይህ ታዲያ ለምን አስፈለገ?

ምክንያቱም ቤተክርስቲያን ከልጅነት ደረጃዋ አልፋለች፣ አሁን ጎልምሳለች፡፡ በመግቢያ ጥቅሳችን እንዳየነው እግዚአብሔር ጽዮንን ሲሰራት በክብሩ ይገለጣል፡፡ ይህ ለሚመጣ ትውልድ ይጻፋል፡፡ ይህ የመጨረሻው ትውልድ ነው፣ የእግዚአብሔርን ክብር በምድር ላይ ለመግለጥ የተጠራ ትውልድ ነው፡፡ ምድር ይህንን ነው ስትጠብቅ የኖረችው፡፡ ሮሜ 8፡ 19 እንዲህ ይላል፡- "የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ

ይጠባበቃልና"፡፡ አሁን በግዛት ስፍራችን ላይ ስለሆንን በአለማችን ላይ በእግዚአብሔር ክብር ተጽዕኖ እናመጣለን፡፡

## የእምነት አዋጅ

ቃሉን ባሰላሰልኩ ጊዜ ያለማቋረጥ እየተቀየርኩ ነው፣ በእግዚአብሔር ክብር ብቻ የምመላለስ ብቻ ሳይሆን እኔ የእግዚአብሔር ክብር ነኝ፡፡ በዚህ ክብር ዛሬ በአለሜ ላይ ተጽእኖ አሳርፋለሁ፤ በጎ ያልሆኑ ሁኔታዎችን እቀይራለሁ፤ በጨለማ አለምም ላይ ሁልጊዜ አበራለሁ፡፡ ፈጽሞ አልሸነፍም! ሀሌሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

የዮሐንስ ወንጌል 17:22; 2 ቆሮንጦስ 3:18; ትንቢተ ኢሳያስ 60:1-2

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 26:1-30 & ኦሪት ዘጸአት 32-33

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 13:1-9 & ኦሪት ዘፍጥረት 38

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ



## ሰኞ 8

# ቋሚ የምህረት መቀመጫ አላችሁ

> እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው (ሮሜ 3፡25)፡፡

አንዳንዶች የኃጢአትን ስርየት ለማግኘት ብዙ አይነት ስርአቶችን ይፈጽማሉ፡፡ አንዳንዶች በራሳቸው ደም ወይም መከራ ለኃጢአታቸው ክፍያ ለመክፈል ራሳቸውን ያሰቃያሉ፡፡ ይህ ሁሉ ግን ከንቱ ነው፡፡ መንገዳችሁ ወይም ልምምዳችሁ እንዲህ ከሆነ አሁኑኑ አቁሙ፡፡ ትግላችሁን አቁሙ! ኢየሱስ ከፍሎላችኋል፡፡

እርሱ ለኃጢአታችሁ መስዋዕት ተደርጎላችኋል፡፡ በመግቢያ ጥቅሳችን "ማስተሰርያ" የሚለው በግሪክ "ሂላስተሪዮን" ሲሆን ትርጓሜውም የምህረት ቦታ ወይም "የምህረት መቀመጫ" ማለት ነው፡፡በብሉይ ኪዳን ማስተሰርያው የታቦቱ መሸፈኛ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ካህናቱን የሚያገኛቸውና መገኘቱም የነበረው በምህረት መቀመጫውሩ ላይ ነበር፡፡

አሁን ግን ለእኛ የእግዚአብሔር የምህረት ስፍራ፣ የምህረት መቀመጫችን፣ የስርየት ማስፈጸሚያው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እግዚአብሔር ኃጢያተኞችን በነጻ ይለቅ ዘንድ ጽድቁን ለማሳየት ኢየሱስ የኃጢአት ማስተሰሪያ ለመሆን መቷል፡፡ እናንተ ዘላለማዊ የምህረት መቀመጫ አላችሁ፣ ያም ክርስቶስ ኢየሱስ ነው! ይህ በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናቱ በየአመቱ ከሚያደርጉት ስርየት የተለየ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናቱ የህዝቡን ኃጢአት በመስዋዕቱ ወይፈንና በሚለቀቀው ፍየል ላይ ይናዘዛሉ፡፡ ነገር ግን በሚቀጥለው አመት የኃጢአታቸው መታሰቢያ ይሆናል፤ ያለፈው ኃጢአታቸው ሊሻር አይችልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "ነገር ግን በዚያ መስዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና" (ዕብራውያን 10፡3-4)፡፡

ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ በሐዋርያት 13፡38-39 እንዲህ ብሏል፡- "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣በእርሱ በኩል የኃጢአት ስርየት እንዲነገርላችሁ፣በሙሴም ህግ ትጸድቁበት ዘንድ ከማይቻላችሁ ሁሉ

ያመነ ሁሉ በእርሱ እንዲጸድቅ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን”፡፡ ከእንግዲህ የኃጢአት መታሰቢያ እንዳይሆን ኢየሱስ ለሁልጊዜና ለዘላለም የሚሆን ፍጹም የሆነ መስዋዕት ለእግዚአብሔር አቅርቧል፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ይህ ነው! ይህንን ለራሳችሁ ተቀበሉና በዙሪያችሁ ላሉ ለሌሎች ስበኩ፡፡እግዚአብሔር ይመስገን!

## የእምነት አዋጅ

በደሙ ማስተሰርያ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ጸድቄያለሁ እንዲያው በነጻ ጻድቅ ተደርጌያለሁ! እርሱ የምህረት መቀመጫያዬ ነው፡፡ በእርሱ ምህረትና ጸጋ በክርስቶስ ስለተወለድኩ እንደ ጽድቅ ተቆጥሮልኛል፡፡ኢየሱስ ለኃጢአቴ ሞቶ በነጻ እንድለቀቅ ከሙታን ስለተነሳ “ነጻ” ነህ ተብያለሁ፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ዕብራውያን 10:11-14; ገላትያ 4:4-5; ሮሜ 4:25

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 26:31-56 & ኦሪት ዘጸአት 34-35

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 13:10-23 & ኦሪት ዘፍጥረት 39

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ማክሰኞ 9

# መንፈስ ቅዱስ፣ የክርስትና ክብር

> እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፣በመንፈስ እንጅ በሥጋ አይደላችሁም፡፡የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም (ሮሜ 8፡9)፡፡

ያለ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ የክርስትና ህይወት መኖር አይቻልም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የክርስትና ክብር ነው፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን ማወቅም ሆነ ኢየሱስን መውደድ አይቻልም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ክርስቲያኖች ለሰይጣን ጥቃት፣ ማታለልና ብዝበዛ የተጋለጡ ናቸው፡፡

ኢየሱስ በማቴዎስ 12፡43-44 መንፈስ ቅዱስ የሌለው ሰው ሁኔታ እንዴት እንደሚሆን እንዲህ ሲል አስተምሮናል "ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፣ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፣ አያገኝምም፡፡ በዚያን ጊዜም፣ ወደ መጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል"፡፡

ዳግም ተወልዶ መንፈስ ቅዱስን ያልተቀበለ ሰው መንፈሱ ተጠርጎና አጊጧል ነገር ግን ባዶ ነው፡፡ ስለሆነም በፈተናና በኃጢአት በቀላሉ ይወድቃል፡፡ ስጋዊ መሻቱን መቆጣጠር ወይም ከክፉ ራሱን መከላከል አይችልም፡፡ የሥጋን ስራና መሻት ማሸነፍ የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡"እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤በመንፈስ ግን ሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁና" (ሮሜ 8፡13)

ያለ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ባህሪ አይኖራችሁም፡፡ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ነበረው፣ሐዋርያቶች መንፈስ ቅዱስ ነበራቸው፡፡ ሕይወት ያለ መንፈስ ቅዱስ ባዶ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን ካልተቀበላችሁ አሁኑኑ ተቀበሉ፡፡ በቀላሉ እንዲህ በሉ፡- "የተባረከ መንፈስ ቅዱስ አሁን በመንፈሴ እቀበልሀለው" እናም በልሳን መናገር ጀምሩ፡፡

## ጸሎት

እጅግ ውድ የሆንከው መንፈስ ቅዱስ፣ ከአንተ ጋር ህብረት እንዳደርግ ስለሰጠኸኝ መብት አመሰግናለሁ፡፡ በማያቋርጥ እድገት፣መጨረሻ በሌለው የስኬትና የድል ጎዳና ላይ አስቀምጠኸኛል፡፡የክርስትና መንገዴ ውብና ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን በማድረግ በሕይወቴ ፍሬ እንዳፈራና ውጤታማ እንድሆን አድርገኸኛል፡፡ አንተን የማያውቁ ሁሉ በሕይወታቸው ያለውን የአንተን አገልግሎት መረዳት እንዲሆንላቸው እጸልያለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡ ፡አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሐዋርያት ስራ 19:2-6; የዮሐንስ ወንጌል 14:16-17

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 26:57-75 & ኦሪት ዘጸአት 36-37

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 13:24-33 & ኦሪት ዘፍጥረት 40

**Leave comments on today's devotional at *www.rhapsodyofrealities.org***



## ረቡዕ 10

# ለበሽታ የማይበገር

> ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል (ሮሜ 8፡11)፡፡

ክርስቲያኖች ነን ስንል በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የምናመልክ ነን እያልን አይደለም፡፡ኢየሱስ በዮሐንስ 15፡5 እንዲህ አለ "እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፤እኔ በእናንተ እናንተም በእኔ ውስጥ አላችሁ"፤ ይህ የጋራ አኗኗር ነው! ይህ ለእግዚአብሔር እውን እንደሆነ ሁሉ ለእናንተም እውን እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ እናንተ ተራ ሰዎች አይደላችሁም፡፡ ዳግም ስትወለዱና መንፈስ ቅዱስን ስትቀበሉ የተሰጣችሁ ሕይወት በህመም፣ በበሽታና በጎዶሎነት ፈጽሞ ሊጠፋ አይችልም፡፡

ከአመታት በፊት "የመንፈስ ቅዱስ ተፅዕኖ በሰው አካል ላይ" በሚል ርዕስ አካፍዬ ነበር፡፡የመንፈስ ቅዱስ መገኘት በሰው አካል ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችሁ ሲኖር አካላችሁ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ቆላስይስ 1፡27 እንዲህ ይላል፡- "...የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው" (ሮሜ 8፡10)፤ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ሲኖር የሚያመጣውን አንደምታ ያሳየናል፡- "ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፣መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው"፡፡

ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው የሚለው ሀይማኖታዊ አባባልና ትርጉም አልባ እንዳልሆነ እግዚአብሔር እንድትረዱት ይፈልጋል፡፡ አሁን ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው፣ ሰውነታችሁ ህያው የሆነው በመንፈስ ቅዱስ እንጅ በደም ዝውውር አይደለም፡፡ ዘላለማዊ የሚያደርጋችሁ ይህ ነው፡፡ለበሽታ፣ ለህመምና ለጉስቁልና የማትበገሩ ናችሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎችን የሚያጠቃው

ኢንፌክሽን ደምን ይበክላል፤ ምክንያቱም ደግሞ የሰው አካል በደም ሕይወት መኖሩ ነው፡፡ ዳግም ስትወለዱ ግን አካላችሁ በደም ህይወት አይኖርም፡፡ ስጋችሁ የሚኖረው በመንፈስ ሀይል ነው፡፡ መክፈቻ ጥቅሳችንን ደግማችሁ አንብቡትና ማንነታችሁን እና በክርስቶስ ምን የእናንተ እንደሆነ መርምሩ፡፡

አሁን ዳግም ተወልዳችኋል፤ መንፈስ ቅዱስንም ተቀብላችኋልና ከዚህ በኋላ ፈጽሞ ልትታመሙ አይገባችሁም! ሰውነታችሁን ለህመም ፈጽሞ አሳልፋችሁ አትስጡ፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ሰውነታችሁን አስገዙ፡፡

## የእምነት አዋጅ

በሰውነቴ ላይ ሊመጣ የሚችለውን የትኛውንም ህመም ኢየሱስ ተሸክሞልኛል፡፡ በከንፈሬ ባለው የእግዚአብሔር ቃል በክርስቶስ ያገኘሁትን ድል አስጠብቃለሁ! የእግዚአብሔር ሕይወትና ተፈጥሮ ስላለኝ ከህመም፣ ከበሽታና ከጉስቁልና ነጻ ነኝ፡፡ እኔ የማልሞት ህያው ነኝ፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

## ለተጨማሪ ጥናት:

የሉቃስ ወንጌል 10:19; ትንቢተ ኢሳያስ 33:24; መጽሀፈ ምሳሌ 4:20-22

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 27:1-26 & ኦሪት ዘጸአት 38-39

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 13:34-43 & ኦሪት ዘፍጥረት 41

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## ሐሙስ 11

# የብርሃናት ምስጢር

> ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም (ዮሐንስ 1፡5)፡፡

ሐዋሪያው ዮሐንስ በስጋ ስለተገለጠው ቃል መገለጥን ሰጥቶናል፡፡ እርሱ (ቃሉ እራሱ) እንዴት በምድር ላይ እንደመጣ ገልጾልናል፤ አለም ግን አላወቀውም፡፡ በማያሻማ ሁኔታ የእግዚአብሄር ቃል ህይወት እንደሆነ ነግሮናል፣ ይህ ህይወት ደግሞ የሰዎች ብርሃን ነው!

ቁጥር አምስት ላይ እንዲህ ብሎ ቀጠለ “ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም አላሸነፈውም” “አላሸነፈውም” የሚለው ቃል ሲሆን በግሪክ “ካታላንባኖ” ተብሎ ተተርጉሟል፣ ትርጓሜውም ጓግቶ መውሰድ፣ ማግኘት እና ድል ማድረግ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ጨለማ ብርሃንን ሊቆጣጠረው፤ ድል ሊያደርገው፣ ሊይዘውም አልቻለም ማለት ነው፡፡

ጨለማ ብርሃንን ድል ሊያደርገው አልቻለም ወይንም የብርሃናትን ምስጢር አልተረዳውም፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ጨለማ ብርሃንን ድል ሊያደርግ ወይም ሊያሸንፈው አልተቻለውም፡፡ አንድ ክፍል ውስጥ ብርሃንን ማብራት ፈልጋችሁ፣ ከጨለማው ድቅድቅነት የተነሳ የብርሃኑን ኃይል ሲያሸሸው አጋጥሟችሁ ያውቃል? ይህ ሊሆን አይችልም! የፈለገ ጨለማው ብርቱ ቢሆን፣ ከብርሃኑ ሊበልጥ አይችልም፡፡ የብርሃኑ ኃይል የብልጭታ ያክል ትንሽ እንኳን ቢሆን፣ ጨለማው ይሸሻል፡፡

ይህ እውነታ ኢየሱስ እናንተን “የዓለም ብርሃን ናችሁ” ሲላችሁ ለመረዳት ያስችላችኋል (ማቴዎስ 5፡14)፡፡ የተናገረው እንደ ክርስቲያን ስላላችሁ ጥሪ ነው፣ ይህንን እውነት ልታውቁ ይገባል፡፡ የተጠራችሁት አለማችሁ ላይ ባለው ጨለማ ላይ እንድታበሩ ነው ፤ የተጠራችሁት ግዛታችሁ ላይ እንድታበሩ ነው፤ እናንተ ጨለማ ሊቋቋመው የማይችለው ብርሃን ናችሁ፡፡

ምናልባትም ተማሪ፣ የደህንነት ሰራተኛ፣ የህግ ባለሙያ፣ የባንክ

ሠራተኛ፣ ዶክተሮች ወይም ሳይንቲስቶች ልትሆኑ ትችላላችሁ፣ በሙያችሁ ስፍራ ባሉት ላይ እናንተ ብርሃን ናችሁ፡፡ በአንድ ነገር ዙሪያ የበዛ ጨለማ ካለ፣ ያንን ጨለማ ማስወገድ ያለባችሁ እናንተ ናችሁ፣ መልሱ ያለው ከእናንተ ዘንድ ነው፣ በእዛ መስክ ላይ ብርሃን መሆን የምትችሉት እናንተ ናችሁ፡፡ ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆኑ ሃሳቦች እና ልቀት በተሞላበት አስተሳሰብ የሚያስፈልገውን መፍትሄ የምትሰጡት እናንተ ናችሁ፡፡

ዓለማችሁን ዛሬ አቀጣጥሉት “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ” (ማቴዎስ 5፡16)፡፡

## የእምነት አዋጅ

ባለሁበት ስፍራ በሙሉ፣ በምሰራው ስራ በሙሉ፣ ብርሃኔ ዓለም እስከሚያስተውል ድረስ ደምቆ ያበራል፣ የእግዚሃብሄርን ክብር በግልጽ እገልጻለሁ፣ በኢየሱስ ስም ጨለማን ከአካባቢዬ አስወግዳለሁ፡፡ አሜን!

## ለተጨማሪ ጥናት:

የማቴዎስ ወንጌል 5:16; ኤፌሶን 5:13

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 27:27-44 & ኦሪት ዘጸአት 40

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 13:44-52 & ኦሪት ዘፍጥረት 42

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



አርብ 12

# በጸሎት መትጋት

> የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች (ያዕቆብ 5፡16)፡፡

ቀለል ያለው ትርጓሜ የመግቢያ ጥቅሳችንን እንዲህ ይተረጉመዋል "የማያቋርጥ ከልብ የሆነ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፡፡" "የማያቋርጥ" የሚለው ቃል ተከታታይ የሆነ ነገር መኖር እንዳለበት ያመለክታል፡፡ ጥቂት ቃላትን ብቻ ተናግራችሁ ሁኔታው "አልቋል ተጠናቋል" ማለት አትችሉም፡፡ መንፈሳችሁ ድልን እንዳደረጋችሁ እስከሚያሳውቃችሁ ድረስ መግፋት አለባችሁ፡፡

እስኪ ጌታችን ያደረገውን እንመልከት፣ በአንድ ወቅት ለእርሱ ቅርብ የሆኑትን ሶስቱን ደቀመዛሙርቱን - ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና ያቆብን ይዞ ለጸሎት ወደ ጌቴሴማኒ ወጣ፣ ማቴዎስ 26፡39 ይህንን ይነግረናል "ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፦ አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ"

ሉቃስ በመንፈስ እንደዚህ ገልጾታል "በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ" (ሉቃስ 22፡44)፡፡ ኢየሱስ በጣም ተጨንቆ ነበር፣ ስለሆነም አብዝቶ ጸለየ፡፡ ይህ ድንገት የምንጸልየው የሁለት ደቂቃ ጸሎት አይደለም! አስታውሱ ደቀ መዛሙርቱን ለአንድ ሰአት ያክል ከእርሱ ጋር ለመቆየት (ለመጸለይ) አልቻላችሁም ብሎ ተናግሯቸዋል (ማቴዎስ 26፡40)፡፡

ጌታ በጸሎት የጸናው የነበረበትን ሁኔታ ስለሚያውቅ ነው፡፡ የሚጸልይበት ነገር ከእርሱ በላይ ነው፣ ከአባቱ ጋር መለየትን ሊቋቋም ይገባው ነበር፣ ጥያቄው ስለትውልዶች መዳን ነው፣ ስላለፈው፣ ስላሁኑ እና ስለሚመጣው ትውልድ መዳን ነበር፡፡ ለሄዱት በሙሉ፣ በአሁን ዘመን ለሚኖሩት፣ ወደ ፊት ለሚኖሩት፣ ማለትም ዘላለምን እየተመለከተ ነበር፤ ስለሆነም በትጋት ጸለየ፣ አብዝቶ ጸለየ፡፡

ዛሬ ከእኛ የሚጠበቀው ይህ ነው፣ ሁኔታው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ

አስጊ መሆኑን አስተውሉ፣ ለሰዎች ነፍስ መታገል አለብን፣ ለመዳናቸው በጸሎት መትጋት አለብን፣ የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ እስኪመጣ ድረስ የመጨረሻዋ ነፍስ እስከምትድን ድረስ አለማቋረጥ መጸለይ እና መማለድ ይገባናል፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ጠንካራና አሸናፊ የሆነ የጸሎት ህይወት እንድገነባ ስለረዳኸኝ አመሰግናለሁ፣ አሁን ለብዙና በርካታ ወደ መንግስትህ መጉረፍ እጸልያለሁ፣ ክብርህ ዛሬ ምድርን ይሸፍናታል፣ እናም ያልዳኑትን ከጨለማ ወደ ብርሃን ወደ እግዚሃብሄር ልጆችም የከበረ ነጻነት እያመጣ፣ የወንጌልህ ብርሃን ተጽእኖ ይፈጥርባቸዋል፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 ጢሞቴዎስ 2:8; የሉቃስ ወንጌል 18:1-5

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 27:45-66 & ኦሪት ዘሌዋውያን 1-3

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 13:53-58 & ኦሪት ዘፍጥረት 43

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## ቅዳሜ 13

# በመጀመሪያ ኃይሉ አግኙ

> የማያቋርጥ ከልብ የሆነ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች (ያዕቆብ 5፡16)

የማያቋርጥ ከልብ የሆነ ጸሎትን ብዙዎች አይረዱትም፡፡ በጸሎት ጊዜ ከማሳለፋቸው በፊት አዋጆችን ያውጃሉ፣ ከዛም ለምን ጸሎታቸው እንዳልተሳካ በማሰብ ይጨነቃሉ፡፡ በመጀመሪያ እንዴት ኃይልን ማግኘት እንደሚቻል ማወቅ አለባችሁ!

ኃይልን ካገኛችሁ በኋላ፣ የምትፈልጉት ለውጥ የጸና ይሆን ዘንድ፣ ቀጥላችሁ የእምነት አዋጆችን አውጁ፡፡ በ1ኛ ነገስት 17-18 የኤሊያስን ታሪክ አንብቡት፤ ድርቅ እንዲመጣ ጸልዮ ነበር፤ ዝናብም አልዘነበም፤ ለሶስት አመት ተኩል አንድም ጠብታ አልነበረም፡፡ ድርቁ መቆም በሚገባው ጊዜ፣ ኤሊያስ ለጌታ ጥያቄን አቀረበ፡፡ በጸሎት ያሳለፈው አጭር እና ጥቂት ጊዜ ብቻ አልነበረም፤ በፍጹም! ጸሎቱ ቅን፣ ከልብ፣ ብርቱ እና ጥልቅ ነበር፡፡

እየጸለየ መልስን እየተጠባበቀ ምልክትን እንዲያይለት አገልጋዩን ስድስት ጊዜ ልኮት ነበር፣ በሰባተኛው ጊዜ አገልጋዩ በመምጣት እንዲህ አለ "የተጨበጠ መዳፍ የምታክል ደመና ከባህሩ ስትወጣ ትታየኛለች" ኤሊያስ የፈለገው ይህንን ነበር፣ እንዳሸነፈ አውቆ ነበር!

አገልጋዩን እንዲህ ብሎ ነገረው "ወጥተህ አክዓብን፡- ዝናብ እንዳይከለክልህ ሰረገላን ጭነህ ውረድ በለው አለ" (1ኛ ነገስት 18፡44)፡፡ ቅደም ተከተሉን አስተውሉ፣ ኤሊያስ አስቀድሞ ከልብ በሆነ ጸሎት የበዛ ኃይልን አገኘ፣ ከዛም ቃልን አወጣ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ እናንተም በቤታችሁ የመንፈስ ቅዱስን ማዕበል ካነሳሳችሁ በኋላ፤ "ሬማ" የሆነውን ቃል የምታወጡት ያኔ ነው፡፡ ክስተቶችን ወደ እግዚሃብሄር መለኮታዊ እቅድ፣ አላማ እና ፈቃድ ለህይወታችሁ፣ ለቤተሰባችሁ፣ ለከተማችሁ፣ ለሃገራችሁ እና ለአለማችሁ በእርግጠኝነት የምትቀይሩት መንገድ ይህ ነው፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ ዛሬ በአለም ላይ ባሉ ሃገሮች ሁሉ ፍቃድህ እና አላማህ በሁሉም ቦታ ይጸና ዘንድ እጸልያለሁ፡፡ በመሪነት ላይ ያሉ እና በስልጣን ላይ ያሉት ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንዲያደርጉ እና እንዲከተሉ ልባቸው የተሰጠ ይሁን፡፡ ልባቸው ደግሞ ለክፉት የተነሳሱት ኃይላቸው እና ተጽዕኖአቸው የከሸፈ ይሁን፣ ፍላጎታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አይከናወን! በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቤተ-ክርስቲያን የበላይ ትሆናለች፤ ታሸንፋለችም፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ያዕቆብ 5:16-18 AMPC; 1 መጽሀፈ ነገስት 18:41-44

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 28 & ኦሪት ዘሌዋውያን 4-5

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 14:1-10 & ኦሪት ዘፍጥረት 44

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



እሁድ 14

# ለእርሱ ክብር አድርጉት

ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር (ፊልጵስዮስ 2፡3)፡፡

ቀለል ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህንን ሃሳብ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ እንደዚህ ይላል "ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ (ለሁከት፣ በጠብ፣ በራስ ወዳድነት፣ ወይም በማይጠቅም አላማ) ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፡፡" ይህ በ1ኛ ነገስት ላይ ያለውን በነብዩ ኤሊያስ እና የበዓል ሃሰተኛ ነብዮች መካከል ያለውን ግድድር ያስታውሰናል፡፡

አንዳንድ ይህንን ክፍል በጥድፊያ ያጠኑ ሰዎች፣ ኤሊያስ ይህንን ያደረገው በሌሎች ዘንድ ራሱን ከፍ ለማድረግ ብሎ እንዳደረገው ያስባሉ፣ ግን ይህ እውነት አይደለም፡፡ ነብዩ ንጉስ አክዓብን እስራኤላዊያንን እና የአማልክቶች የሀሰት ነብያትን ማለትም የበአል አራት መቶ ሃምሳ ነቢያት እና የአሽራህ አራት መቶ ነብያትን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ እንዲሰበስብ ተገዳደረው፡፡ መስዋእትን አቀረቡ እና ከሰማይ እሳትን አውርደው መስዋእቱን እንዲበላ አደረጉ፡፡ በዚህ ተግዳሮት ያሸነፈው እውነተኛ ነብይ ይባል ነበር፡፡

እያንዳንዱም በመሰዊያው ስፍራ በሬ አዘጋጁ እና ከሰማይ እሳት እንዲያወርድ አማልእክታቸውን ጠሩ፡፡ የበአል ነብያት ብዙ ጮሁ አለቀሱ ምንም ነገር ግን ከሰማይ አልወረደም፡፡ የኤሊያስ ተራ ሲሆን ኤሊያስ መስዋእቱን በውሃ አራሰው፡፡ ከዚያም እግዚሃብሄርን ጠራ እና እግዚሃብሄርም እሳትን ከሰማይ ላከ፣ እሳቱም ሙሉ በሙሉ መስዋእቱን በላው፡፡

በ1ኛ ነገስት 18፡36 ላይ ያለውን የኤሊያስን ቃል አንብቡ፤ "አቤቱ፥ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፥ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ፥ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ፥ ይህንም ሁሉ በቃልህ

እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ”፡፡ የእግዚሃብሄርን መንፈስ ምሪት እየተከተለ ነበር፣ ይህ ድፍረት የተሞላ ተግባሩ የራሱን ኃይል ለማሳየት አልነበረም፣ በእግዚአብሄር ምሪት ብቻ መሰረት አድርጎ የፈጸመው ነው፡፡

ውጤቱን ተመልከቱ፣ እስራኤላዊያን በአክዓብ ማመንን ትተው በኤሊያስ አምላክ ሉአላዊነት አመኑ፡፡ ኤሊያስ ያደረገው ነገር የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሄርን በህዝቡ ፊት አከበረው፡፡ ለእግዚሃብሄር የምታደርጉት ማንኛውም ነገር ራስ ወዳድ ከሆነ ምኞት ወይም ከትዕቢት የተነሳ አይሁን፣ ለእርሱ ክብር መሆን አለበት፡፡ ልክ እንደ ኤሊያስ፣ በቃሉ መሰረትና በቃሉ አማካኝነት መንፈስን ቅዱስን መከተል ተማሩ፡፡ ከዚያ ስራችሁም ሆነ መንገዳችሁ ሁሉ ጌታን ያከብራል፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ ቃልህ ሃሳቤን፣ እቅዴን እና ውሳኔዬን የሚመራ ብርሃን ነው፣ በህይወትም በክብር እንድራመድ ያደርገኛል፣ ምሪትህን ከትምክህት ነጻ በሆነ ልብ እከተላለሁ፣ በቃልህ አማካኝነት አቅጣጫን፣ መገለጥን እና ስለመንግስትህ ምስጢራትና እውነታዎች እይታን እቀበላለሁ፤ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

1 መጽሀፈ ነገስት 18:30-39

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 1:1-20 & ኦሪት ዘሌዋውያን 6-7

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 14:11-21 & ኦሪት ዘፍጥረት 45

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ



ሰኞ **15**

## ለጸሎት የበለጠ ትኩረት ስጡ

> እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች (ያዕቆብ 5፡16)፡፡

ማቴዎስ 17 ደቀመዛሙርቱ ሊፈውሱት ስላልቻሉት ስለ አንድ የሚጥል በሽታ ስላለበት ልጅ ይነግረናል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር በመጨረሻም አባቱ ወደ ኢየሱስ እንዳመጣው እና “ኢየሱስም ገሠጸው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፥ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ” (ማቴዎስ 17፡18) ይላል፡፡

ደቀመዛሙርቱም በመደነቅ ለብቻቸው ወደ ኢየሱስ በመሄድ ለምን ሊያስወጡት እንዳልቻሉ ጠየቁት፡፡ ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው “ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፡- ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም። ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው” (ማቴዎስ 17፡20-21)፡፡

ለአንዳንድ ነገሮች እንዴት መዘጋጀት እንዳለብን የኢየሱስ መልስ ያስተምረናል፡፡ ስለዚህ በመንፈስ ለመፍጠር የምትፈልጉት ተጽእኖ፣ ለጸሎት በሰጣችሁት ትኩረት መጠን ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ አንድን ነገር እውን ለማድረግ ስትፈልጉ፣ ያ በእርግጥም የበለጠ ጊዜ የሚወስድ ብርቱ የሆነ የጸሎት ህብረት ማድረግን ይጠይቃል፡፡

ከጌታ ጋር ጊዜን ለማሳለፍ፣ ሁሉንም ነገር እና ማንኛውንም ሰው ዘግታችሁ፣ የግል የጸሎት ጊዜ ሊኖራችሁ እንደሚገባ አጽንዖት ከምንሰጥባቸው ምክንያቶችም አንዱ ይህ ነው፡፡ የታቀደ እና ጠንካራ የጸሎት ስርአት ሊኖራችሁ ያስፈልጋል፤ ከጌታ ጋር ለሚኖራችሁ የግል ህብረት፣ የሚረብሻችሁን ነገር አስወግዳችሁ የተለየ ጊዜን አቅዱ፡፡ በተለይም በዚህ በመጨረሻ ዘመን፣ ለዚህ የበለጠ ትኩረት ስጡ፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በእነኚህ የህብረት ጊዜዎች፣ በጸሎት ለውጥን ለማምጣት ስለተሰጠኝ እድል አመሰግንሃለሁ፡፡ አዕምሮአቸውን የጋረደው እንዲነሳ እና ወንጌልን እንዲቀበሉ በአለም ላይ ስለጠፉት ነፍሶች እጸልያለሁ፡፡ እንዲሁም የወንጌል አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ እና ብዙ ጻድቃኖች ለዚህ ታላቅ ስራ ፍጹማን እንዲሆኑ እጸልያለሁ፣ በኢየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

ትንቢተ ኤርምያስ 29:12; ኤፌሶን 6:18 AMPC

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 1:21-45 & ኦሪት ዘሌዋውያን 8

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 14:22-33 & ኦሪት ዘፍጥረት 46

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## ማክሰኞ 16

# የበለጠ እውቀት ጨምሩ

> የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15)፡፡

እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤ አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።" (ሆሴዕ 4፡6)። ለእያንዳንዳችን የእግዚአብሔር ቃል እውቀት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በየትኛውም አጋጣሚ፣ ትክክለኛ የሆነ የቃሉ ዕውቀት እንዲኖራችሁ የግድ መፈለግ አለባችሁ፤ ለዚህ ምንም ሌላ አማራጭ የለም።

የእግዚአብሔር ፈቃዱ፣ ተፈጥሮው እና አላማው በቃሉ ውስጥ ተገልጠዋል። የእርሱን ቃል ችላ ማለት፣ የአብን ፈቃድ እና እርሱ እናንተ እንድትኖሩት ስለሚፈልገው ነገር ጨለማ ውስጥ መሆን ማለት ነው። በግላችሁ በምታጠኑበት እናንተን የሚረዱ በርካታ ማጥኛ መሳሪያዎችን አዘጋጅተንላችኋል። ለምሳሌ ራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ፣ በየቀኑ ለእናንተ ከእግዚአብሔር ቃል አዳዲስ ዕይታ በማምጣት፣ የመንፈሳዊ ህይወት እድገታችሁን ለማሳደግ የተዘጋጀ ህይወታችሁን የምትመሩበት መሳርያ ነው።

የራፕሶዲ የየዕለት አርዕስት፣ የመግቢያ ጥቅስ፣ የየዕለቱ መልዕክት፣ የየዕለቱ የእምነት አዋጅ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ዕቅድ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተዘጋጁ በእናንተ በየቀን ጉዟችሁ ላይ የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ለመስጠት የተቀናበሩ ናቸው። ተጠቀሙበት።

የባለፉትን ዕትሞች መጠቀምም ትችላላችሁ፤ ቃሎቹ አሁንም አዲስ ናቸው፤ አንብቧቸውና አጥኗቸው። አስታውሱ፥ የእግዚአብሔር ቃል ጊዜ የሚያልፍበት አይደለም። ለዛሬም ይጠቅማል።

ሌሎችም የተለያዩ የህይወት ጉዳዮችን የሚሸፍኑ እጅግ በርካታ የመማርያ መሳሪያዎች በድምጽም በምስልም በፓስተር ክሪስ ዲጅታል ላይብረሪ (ፐሲድኤል) ላይ ታገኛላችሁ። እነዚህ ማስተማሪያዎች እንዲኗርዋችሁ አድርጉ፤ እምነታችሁም በፍጥነትና በስፋት እንዴት

እንደሚያድግ አይታችሁ ትደነቃላችሁ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል በግል ማጥናትን ከየዕለት ዕለት ልምምዳችሁ ዋነኛው ተግባር እንዲሆን አድርጉ።

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በክርስቶስ ላለኝ ለከበረው ርስት ልቤን ስለከፈትከው ሀሴት አደርጋለሁ። ልቤ በቀጣይነት በእውቀትና በመንፈሳዊ መረዳት ተጥለቅልቋል። በቃሉ እውቀት አማካኝነት ከማጣት፣ ከህመም፣ ከበሽታ፣ ከሽንፈት፣ እና ከዚህ ዓለም መሰረታዊ መመሪያዎች የበላይ ሆኜ እኖራለሁ። ህይወቴ ወደላይና ወደፊት ብቻ ነው፤ ከክብር ወደ ክብር፣ ከእምነት ወደ እምነት፣ እናም ከጸጋ ወደ ጸጋ ነው! አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ጴጥሮስ 1:5; የሐዋርያት ስራ 20:32

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 2:1-22 & ኦሪት ዘሌዋውያን 9-10

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 14:34-15:1-9 & ኦሪት ዘፍጥረት 47

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ረቡዕ **17**

# የምትሰሙትን መርምሩ

> *ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና (1ኛ ዮሐንስ 4፡1)፡፡*

ሮሜ 13፡1ን በመጥቀስ አንድ ስልጣን ላይ ያለ ሰው እስከተናገረው ድረስ፣ የተባሉትን ትእዛዛት ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያስቡ አንዳንዶች አሉ። “እርሱ የታወቀ መሪ ነው፤ ስለዚህ የሚናገረው ነገር ሁሉ እውነት መሆን አለበት፤” ይላሉ፡፡ ነገር ግን እንደዚያ አይደለም።

በመጀመሪያ ጥቅሱን በትክክለኛ መንገድ እንየው፤ እንዲህ ይላል፥ “ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው” (ሮሜ 13፡1)። የመክፈቻ ጥቅሳችን የሚነግረን መንፈስን ሁሉ እንድንመረምር ነው። ማንም ሰው በነገራችሁ መሰረት መሮጥ ወይም በማንም የተነገራችሁን ሁሉ ማድረግ የሌለባችሁ ለዚህ ነው፤ ይህ ስልጣን ከየት እንደመጣ መርምሩ። ከሰይጣንም ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ አለባችሁ።

እግዚአብሔር መሪን ሊመርጥ ይችላል ነገር ግን መሪው የማይታመን ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳ በእግዚአብሔር የተመረጡ ቢሆኑም፣ በእግዚአብሔር ላይ በተቃርኖ የተነሱ መሪዎችን በተመለከተ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይገኛሉ። የንጉስ ሳኦልን ታሪክ እንደምሳሌ እንውሰድ። በ1ኛ ነገስት ምዕራፍ 15 ላይ ነቢዩ ሳሙኤል ለንጉስ ሳኦል በጣም ግልጽ የሆነ መመሪያ ሰጠው። አማሌቅን ሄዶ እንዲወጋና እነሱንና የነሱ የተባለ ምንም ሳይስቀር እንዲደመስስ ተናግሮት ነበር!

ሳኦልም እንደታዘዘው ሊያደርግ ወጣ፤ እናም ድል አደረገ። የማይረባውንና ዋጋ ቢስ የሆነውን ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ ደመሰሰ፤ ነገር ግን መልካም እና ዋጋ አላቸው ብሎ የመረጣቸውን አስቀረ፤ ንጉስ አጋግን ብቻ ሳይሆን፣ ከበጎችም ከበሬዎችም ከሁሉም ነገሮች ምርጥ የነበሩትን አስቀረ። የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ነበር?

እርሱም ለነቢዩ ሳሙኤል እንዲህ አለ፤ “...ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት ተጸጸትሁ ብሎ ወደ

ሳሙኤል መጣ። "(1ኛ ሳሙኤል 15፡11)። ይህም እግዚአብሔርን የሚሰሙት እና ትክክል የሆነው ነገር የሚያደርጉት ሁሉም መሪዎች እንዳልሆኑ ያሳያል።

ነገሮችን ሁሉ ለእግዚአብሔር ቃል ብርሃን አስገዙ። 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡21 እንዲህ ይላል፥ "ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ"። አንድ ስልጣን ላይ ያለ ሰው ስለተናገረው ነገር ጥሩ ስሜት ስለተሰማችሁ ብቻ፣ ነገሩ ከእግዚአብሔር ነው ማለት አይደለም። ሁሉን መርምረን የምንዳኝበት ከፍተኛው ስልጣን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ሁልጊዜ አስታውሱ።

መሪዎችም ጭምር፥ እግዚአብሔርን መስማት በጣም አስፈላጊ ነው። እርሱ ምን እንደሚፈልግ እወቁ፣ እናም የእርሱን ፈቃድ አድርጉ። ማመቻመችን እምቢ በሉ። ለእግዚአብሔር እና ለሕዝቡ መልካም መሆናቸውን እርግጠኛ ለመሆን ፖሊሲዎቻችሁን መርምሩ።

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በማንም የታዘዙ ትእዛዛት ቢሆኑም፣ የትኛውንም ትእዛዝ ሆን ብዬ በእግዚአብሔር ቃል እመዝናለሁ፡፡ ለእኔ ህይወትን፣ ብርሃንን፣ አቅጣጫንና አላማን የሚሰጡኝን ትዕዛዛትህን አልቃወምም። እርምጃዎቼ በአንተ፣ በቃልህና በመንፈስህ የተመሩ ናቸው፤ በኢየሱስ ስም። አሜን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

የማቴዎስ ወንጌል 7:15-16; 2 ቆሮንጦስ 11:13-15

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማርቆስ ወንጌል 2:23-3:1-12 & ኦሪት ዘሌዋውያን 11-12

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 15:10-20 & ኦሪት ዘፍጥረት 48

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ሐሙስ 18

# በእናንተ ውስጥ ነው

> እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥ (ኤፌሶን 3፡20)፡፡

አንዳንድ ሰዎች በህይወታቸው እና በዓለም ለሚፈጠሩ ክስተቶች እግዚአብሔርን ይወቅሳሉ፤ ይህን የሚያደርጉት ደግሞ እውቀት ማጣት የተነሳ ነው። እግዚአብሔር ሃያል ነው፤ ነገር ግን እናንተ የምትፈልጉትን ተአምራት ለማግኘት እና ለዛም የሚያስፈልጋችሁ ሃይል ያለው በእናንተ ውስጥ ነው፤ ከእናንተ የሚጠበቀው ያንን በስራ ላይ ማዋል ብቻ ነው።

የመከፈቻ ጥቅሳችንን በጥንቃቄ አንብቡት፤ "እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥..." ይላል። እግዚአብሔር በህይወታችሁ የሚሰራው ማንኛውም ነገር የሚወሰነው በእናንተ ውስጥ ባለው የእርሱ ሃይል መጠን ነው። ስለዚህ በእውነቱ በህይወታችሁ ለሚሆኑ ነገሮች ሁሉ እርሱን ተጠያቂ ልታደርጉም አትችሉም፣ ማድረግም የለባችሁም።

በህይወታችሁ የእርሱ ቃል እንዳይፈጸም "የሚያዘገየውም" እርሱ አይደለም፤ በውስጣችሁ ያለውን ሃይል ማንቀሳቀስ ያለባችሁ እናንተ ራሳችሁ ናችሁ። የምትፈልጉት ነገር ምን ይሁን ምን ግድ አይልም፤ ፈውስ ይሁን፣ በገንዘብ መጨመር ይሁን፣ አዲስ ስራ ይሁን፣ ልጅ ይሁን፣ በአገልግሎት እድገት እና መስፋት ይሁን፣ ንግድ ወይም የራሳችሁ ስራ ይሁን፣ በትምህርታችሁ መሳካት ይሁን ወዘተ፣ ያንን ማድረግ የሚችለው ሀይል በእናንተ ውስጥ ነው። ጌታ ኢየሱስ በሐዋሪያት ስራ 1፡8 ላይ እንዲህ አለ፤ "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥..."፡፡ ያ ሀይል ነገሮችን መቀየር የሚችል ነው፤ እናም ያንን

ማንቀሳቀስ የሚቻልበት ፈጣኑ መንገድ በልሳን መናገር ነው።

1ኛ ቆሮንቶስ 14፡4 እንዲህ ይላል፤ “በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤...” ይህ ማለት በልሳን የሚጸልይ ልዕለ-ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ራሱን በሃይል ያነቃቃል ወይም ያነሳሳል፤ ከውስጡ መልኮታዊ ሀይልን ያነሳሳል። በተጨማሪም ያ የእግዚአብሔር ሃይል፣ የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት በማወጅም ይነሳሳል።

እግዚአብሔር እና ቃሉ አንድ ናቸው። ምንም አይነት ሁኔታን በተመለከተ ቃሉን ስታውጁ፣ በሁኔታው ላይ ለውጥን ለማምጣት የእርሱን ሃይል እያነሳሳችሁ ነው። በቃሉ ላይ የማሰላሰል፣ የማውጣት የማውረድና አውጥቶ የመናገርን ልምድን አዳብሩ፤ ከዚያም በህይወታችሁ ላይ የእግዚአብሔር ሃይል መለቀቅን ትለማመዳላችሁ።

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ እኔ የምሻውን ለውጥ በህይወቴ ላይ በማምጣት ለሚሰራው ታላቅ ሀይልህ አመሰግናለሁ። አሁንም እንኳ በክብርህ ተለውጫለሁ፤ በጽድቅና በልህቀት እንድገዛና እንዳስተዳድር እያደረገኝ፣ ቃልህ በህይወቴ ያሸንፋል።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ቆላስያስ 1:29; ሮሜ 8:26-27 AMPC; ኤፌሶን 5:18-19

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማርቆስ ወንጌል 3:13-35 & ኦሪት ዘሌዋውያን 13-14

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 15:21-28 & ኦሪት ዘፍጥረት 49

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



አርብ **19**

## ለአለም የተሰጠ ስጦታ

> ...ስለዚህም ሕይወት የማይዋሽ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ፥በዘመኑም ጊዜ፥ መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ፥ ለእኔ አደራ በተሰጠኝ ስብከት ቃሉን ገለጠ (ቲቶ 1፡2-3)፡፡

ይህ እንዴት የተዋበ ነው፤ አለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ የተስፋ ቃል የነበረው የዘላለም ህይወት፣ አሁን ተፈጽሟል። የእግዚአብሔር አላማ ይህንን በወንጌል ስብከት አማካኝነት ለሰው ማቅረብ ነበር። ይህም ለአለም ሁሉ ስጦታ ነበር። "ዘላለማዊ ህይወት ለክርስቲያኖች ብቻ አይደለም እንዴ?" ልትሉ ትችላላችሁ፤ አይደለም፤ የሐንስ 3፡16 እንዲህ ይላል፤ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡"

ሀጢአተኛ በኢየሱስ ሲያምን እና ጌትነቱን ሲያውጅ እሱ ወይም እሷ የዘላለምን ህይወት ይቀበላሉ፤ እናም ክርስቲያን ይሆናሉ። ያንን ህይወት መቀበላችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ አንድነት፣ ልጅ ወደ መሆን ግንኙነት አምጥቷችኋል። ኢየሱስ በዮሐንስ 5፡26 ላይ እንዲህ አለ፤" አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና"፡፡ ዮሐንስ በመልእክቱ እንዲህ ይነግረናል "እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡" (1ኛ የሐንስ 5፡11-12) ። ኢየሱስ ላለው ሰው የዘላለም ህይወት የአሁን ሰዓት ውርስ ነው፤ "...ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው። ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤"፡፡

ብዙዎች የዘላለም ህይወት ማለት ሳያቋርጥ የሚቀጥል ጊዜ ብቻ አድርገው ይወስዱታል፤ ነገር ግን ያ አንዱ ገጽታው ብቻ ነው። የዘለላም ህይወት ማለት ከፍተኛ የሆነ ህይወትና የእግዚአብሔር ባህሪ ነው፤ ያም

የእግዚአብሄር አይነት ህይወት ነው። ይህም የመለኮታዊነት አንኳር ነው። ይህ በውስጣችሁ ያለ ህይወት በሰይጣን ላይ የበላይ ያደርጋችኋል፤ የእግዚአብሔር ህይወትና ባህሪ ነው፤ ዳግም ስትወለዱ በእናንተ የሰው ህይወት ምትክ የተተካ ነው። ክብር ለእግዚአብሔር ነው!

## የእምነት አዋጅ

የዘላለም ህይወት በውስጤ አለ። ተራ ሰው አይደለሁም፤ መለኮታዊ ህይወት በአካሌ ውስጥ ሁሉ ይንሸራሸራል! እግዚአብሔርን ከሚመስሉ ጋር ህብረት አለኝ፤ ከሰይጣን የበላይ ነኝ፤ ለበሽታ፣ ለህመም እና ለድካም ሁሉ የማልበገር ነኝ። ሃሌ ሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 6:23; የዮሐንስ ወንጌል 10:26-28; የዮሐንስ ወንጌል 17:3

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 4:1-20 & ኦሪት ዘሌዋውያን 15

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 15:29-39 & ኦሪት ዘፍጥረት 50

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## ቅዳሜ 20

# እምነታችሁ ይፈተናል

የትዕግሥቴን ቃል ስለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ። (ራእይ 3:10)፡፡

በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:3 ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤ "ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ከህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና።"

ብዙዎች ከእምነታቸው እንደሚያፈነግጡ ይናገራል፡፡ ይህ ለምን ይሆናል? በመሳፍንት 7 ላይ እግዚአብሔር ጌዴዎን ከምድያማውያን ጋር ለመዋጋት እንዲሄድ በፈለገ ጊዜ እግዚአብሔር (ጌዴዎን) ጠላቶቹን ድል እንደሚያደርግ በመልአኩ አረጋገጠለት፡፡

ጌዴዎን ሰራዊት እንደሚያስፈልገው አሰበ፤ ስለዚህ ወታደሮቹን ሰበሰበ፡፡ እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለው፣ "ከብዙ ወታደሮች ጋር ከሄድክ በራስህ ጦርነቱን ያሸነፍከው ይመስልህ ይሆናል፡፡ የፈሩት ሁሉ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ንገራቸው አለው"፡፡እናም መጽሐፍ ቅዱስ ከእነሱ ውስጥ ሃያ ሁለት ሺህ የሚሆኑት እንደተመለሱ ይናገራል (መሳፍንት 7 3)፡፡ "እግዚአብሔርም ጌዴዎንን፦ ሕዝቡ ገና ብዙ ነው ወደ ውኃ አውርዳቸው፥ በዚያም እፈትናቸዋለሁ፤ ጠላትን በተጠንቀቅ እየጠበቁ ውሃ የጠጡትን ብቻ አስቀር አለው።"

እናም መጽሐፍ ቅዱስ ሶስት መቶዎች ብቻ ያንን ፈተና አለፉ ይላል (መሳፍንት 7 4-6ን አንብቡ)፡፡ እየተፈተኑ መሆናቸውን እንኳን አላወቁም ነበር፡፡ እንዲሁም፣ በኤርምያስ 9 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች አንደበታቸው ሐሰት እንደለመደ ይናገራል፡፡ እነሱ በጣም ሀሰተኞች ስለነበሩ የገዛ ወንድም እንኳን እምነት ሊጣልበት አልቻለም ነበር፡፡ በዚህ ተንኮል እና ግብዝነት እና በውሸት ምክንያት እግዚአብሔር "እነሆ፣ አቀልጣቸዋለሁ እፈትናቸውም አለሁ.... ብሏል" (ኤርምያስ 9፡7)፡፡ ይህ የሚሆነው አሁን ባለንበት የመጨረሻ ቀናቶች ውስጥ ነው፡፡ ታላቅ ፈተና እየመጣ ነው፤ አሁን ተጀምሯል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እውነተኛ የሆኑትን ከሐሰተኞች ማለትም በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጽሞ እውነተኛ ያልነበሩትን መለየት አለበት፡፡

ይህ ጉዳይ አስፈላጊ ባይሆን ኖሮ፤ በመግቢያ ጥቅሳችን ላይ እንደተነበበው ኢየሱስ በፊላደልፊያ ያለችውን ቤተክርስቲያን በመወከል ጣልቃ መግባት ባላስፈለገው ነበር፡፡ በክርስቶስ ላይ ያላችሁ እምነት እውነተኛ ከሆነ፤ እምነታችሁ ይፈተናል፤ “ነገር ግን በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ፥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል።” (1ኛ ጴጥሮስ 1:7)፡፡ በሕይወታችሁ የሚያሳስባችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ እና መንግስቱ ብቻ ይሁን፡፡

## የእምነት አዋጅ

እኔ በክርስቶስ ውስጥ በጥልቀት ሥር የሰደደ መሠረት አለኝ። እኔ የምኖረው የእግዚአብሔርን ሕልም፣ የመንግሥቱን የመስፋፋት ራዕይ እና ወንጌል በዓለም የማሰራጨት ሥራ ለመፈፀም ነው፡፡ እኔ ትኩረቴ ከላይ ባሉት ነገሮች ላይ እንጂ በዚህ ዓለም ጊዜያዊ ደስታ ላይ አይደለም፡፡ የሚገለጥበትን ጊዜ በጉጉት እየጠበቅኩኝ፤ ሳልናወጥ የጌታን ሥራ በደስታ እየሠራሁ፣ ጽኑ ነኝ፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

*መጽሀፈ ኢዮብ* 23:10; *ቆላስያስ* 3:1-2; *የዮሐንስ ራዕይ* 3:9-10 CEV

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 4:21-41 & ኦሪት ዘሌዋውያን 16-18

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 16:1-12 & ኦሪት ዘጸአት 1

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



## እሁድ 21

# አንድ እንጀራ አንድ አካል

> ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ አሉት (ዮሐንስ 6:31)፡፡

በመግቢያ ጥቅሳችን ላይ ያነበብነው ጌታ ኢየሱስ ለአይሁዶች ሲናገር ነበር፡፡ ከቁጥር 32-33 እንዲህ ሲል ይቀጥላል፣ “... እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው።”

በአርባ ዘጠነኛው ጥቅስ ላይ ይህንን ሀሳብ የበለጠ አፅንዖት ሰጠው፤ “አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው።” ሐንስ 6:49-50 ከሰማይ የወረደው ህያው እንጀራ እየሱስ ነው።

ይህንን በዮሐንስ 6:51 ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል አስረዳቸው፤፡ - “ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።” ከዚያም ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10:17 ላይ ይህ ከእኛ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ያብራራል፡- “አንድ እንጀራ ስለ ሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለን።” ከእርሱ ጋር አንድ እንጀራ ከሆንን፤ እርሱ በሥጋ የተገለጠው ቃል እንደሆነው ሁሉ (ዮሐ 1:14)፣ ከቃሉ በመወለዳችን እኛም ተመሳሳይ ሕይወት አለን ማለት ነው (1ኛ ጴጥሮስ 1:23)፡፡

ቆላስይስ 1:18 እንዲህ ይላል፡- “እርሱም (ክርስቶስ) አካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው...”፡፡ ጭንቅላትና እና አካል አንድ አይነት ሕይወት አላቸው፡፡ ህይወቱን ከተካፈልን፤ እኛ ደግሞ የእርሱን ጤና፣ ብልጽግና፣ ጥንካሬ እና ክብር እንካፈላለን ማለት ነው።

እርሱ እኛን “የመለኮታዊ ባሕርዩ ተካፋዮች”፣ እግዚአብሔርን ከሚመስሉ ጋር ህብረት ያላቸው ብሎ ቢጠራን አያስደንቅም። 1ኛ ዮሐንስ

4:17 “...እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።” ይላል፡ ፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ ዓይነት ዘር ናችሁ። ስለዚህ በክብር፣ በጽድቅ፣ በጥንካሬና በግዛት እሱ እንደተመላለሰ ተመላለሱ ። ሃሌሉያ!

## የእምነት አዋጅ

እግዚአብሔር ይመስገን! እኔ እኔ ሕያውና ዘላለማዊ ከሆነው ቃሉ ስለተወለድኩ፣ ከጌታ ጋር አንድ ነኝ! የእኔ ዘሮች መለኮታዊ ናቸው፡፡ እኔ የማልበገር ነኝ፣ ዓለማዊ ከሆኑ ነገሮችም ሁሉ የበላይ ሆኜ እኖራለሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት በሕይወት ግዛት ውስጥ በክብር እነግሣለሁ እናም እገዛለሁ። ሃሌ ሉያ!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ኤፌሶን 5:30; 1 የዮሐንስ ወንጌል 4:17; 1 ቆሮንጦስ 10:17 AMPC

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማርቆስ ወንጌል 5:1-20 & ኦሪት ዘሌዋውያን 19-21

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 16:13-20 & ኦሪት ዘጸአት 2

**Leave comments on today’s devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ



ሰኞ 22

## የምትሆኑት የምትናገሩትን ነው

> እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ፦ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል (ማርቆስ 11:23)፡፡

ሕይወታችሁ ከእናንተ የሚወጡ ቃላት ውጤት ነው፡፡ የመክፈቻ ጥቅሳችን ህይወታችንን በቃላቶቻችን የመቅረፅ አስፈላጊነት ላይ አፅንዖት ይሰጣል፡፡ የቃላት ስጦታ፤ ማለትም የመናገር እና ቃላትን የመፍጠር ችሎታ፣ ለሰው ልጅ ከእግዚአብሄር የተሰጠው በጣም የተዋበ የተፈጥሮ ስጦታ ነው፡፡

ሕይወት ለእናንተ የሚያፈራላችሁ የንግግራችሁን መኸር ነው፤ ይህ ምንም ሌላ አማራጭ የለውም። እንደ ክርስቲያን መናገር መቀጠል አለባችሁ፤ በጤንነት መኖር ከፈለጋችሁ ጤናን ተናገሩ፡፡ በጽድቅ መመላለስ ከፈለጋችሁ እና ሁልጊዜም የጽድቅ ሥራዎችን መስራት ከፈለጋችሁ ታዲያ ጽድቅን ተናገሩ፤ ሁልጊዜ፣ ሆን ብላችሁ፤ “እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነኝ። የጽድቅን ሥራዎች እና ፍሬዎችን አፈራለሁ፡፡”በማለት አውጁ።

ትኖሩት ዘንድ ልትናገሩት የግድ ነው፡፡ እንዲህ፣ “ምንም ካልተናገርኩስ? ህይወቴ ምን ይመስላል?” ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ ያኔም መከር ይኖራችኋል፤ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን፤ መኸሩ የሚሆነው የተሳሳተ ነው ። አንድን የአትክልት ስፍራ ያለአንዳች ተንከባካቢ መተው ማለት ነው፤ አረሞች በእርግጠኝነት በራሳቸው ፈቃድ ያድጋሉ፡፡ በቃላታችሁ እራሳችሁን በድል፣ በግዛት እና በብልጽግና ውስጥ አቆዩ፡፡

እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በክርስቶስ ውስጥ ሙሉ ሕይወት እንዲኖራችሁ እና እንድትደሰቱ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ አስቀድሞ አድርጓል። ነገሮችን በዚያ መንገድ ማቆየት የእናንተ ኃላፊነት ነው፤ ይህም በዋነኝነት የሚሆነው በእናንተ የእምነት ዓዋጅ ነው። ሁልጊዜ ታላቅ ሕይወት እንዳላችሁ እውቅና ስጡ። ወደ ክብር እና በጎነት ፤ የኃይል ሕይወት እና

የሞራል ልህቀት እንደተጠራችሁ አውጁ። እነዚህን መግለጫዎች በየቀኑ አድርጉ፡፡

እናንተ የጎደላችሁ ምንም ነገር የለም (1 ቆሮንቶስ 3፡21 ፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1:3)፣ እናም ማድረግ የማትችሉት ነገር የለም (ፊልጵስዩስ 4 13)። ስለዚህ፣ ሁልጊዜ የተትረፈረፈ፣ ልእለ ተፈጥሯዊ የሆነ አቅርቦት፣ ጥንካሬ፣ ዕድሎች እና ድሎችን አውጁ፤ እናም ህይወታችሁ ወደዚያ አቅጣጫ ብቻ ይሄዳል።

## የእምነት አዋጅ

የእግዚአብሔር ክብር ዛሬ በእኔ ውስጥ ተገልጧል፤ በቃሉ ውስጥ ስመላለስ የጽድቅም ፍሬ ሳፈራ የእርሱ ጥበብ በእኔ ውስጥ ይታያል እናም ይሰማል፡ ፡ የእኔ አቅርቦትና ችሎታ ከተፈጥሮ በላይ ነው። በሕይወቴ ውስጥ ምንም የጎደለ ወይም የተሰበረ ነገር የለም! ክርስቶስ በእኔ ውስጥ ስላለ፤ እኔ ኃይልን ተሞልቻለሁ፤ እርሱ ክብሬ፣ ጽድቄ፣ ጥበቤ፣ ስኬቴ እና ብልጽግናዬ ነው። ስሙ ለዘላለም የተባረከ ይሁን።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ዕብራውያን 11:3; የማቴዎስ ወንጌል 12:36-37 NIV

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 5:21-43 & ኦሪት ዘሌዋውያን 22-23

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 16:21-28 & ኦሪት ዘጸአት 3

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ማክሰኞ 23

# ለክብሩ መኖር

> በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ (2ኛ ቆሮሰቶስ 5:15)፡፡

በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት ግድ የሚል አንድ ነገር ብቻ አለ፤ ለጌታ መኖር፤ ለክብሩ መኖር፤ ዓላማ ያለው ሕይወት መኖር ነው። ኢየሱስ በዚህ ረገድ ልንከተለው የሚገባውን ምሳሌ አሳይቶናል፡፡ "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ (ዮሐንስ 17:4)፡፡

የእናንተም አስተሳሰብ ይህ መሆን አለበት፣ አብን ማክበር የእናንተ ፍላጎት እና የመኖር ዓላማ መሆን አለበት። አብን እንዴት እናከብራለን? የእርሱን ፈቃድ በማድረግ፤ እሱ ለእናንተ የሰጠውን ሥራ በመሥራት እና ሥራውን በማጠናቀቅ ነው። እርሱ ለእናንተ ሕይወት ያውን ዓላማ እውቃችሁታል? የእርሱን ስራ እየሰራችሁ ነው?

የአብ ዓላማ የአለም ሁሉ መዳን ነው፡፡ ኢየሱስን የላከበት ምክንያትም ይህ ነው፡፡ እናም የእናንተም የሕይወት ዓላማ ከዚህ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በህይወታችሁ ምንም ብትሰሩ፣ የጠፉ ነፍሳትን የማትደርሱና የማታሸንፉ ከሆነ፤ ባዶ ሕይወት እየኖራችሁ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲመጣ እንጂ ማንም እንዲጠፉ አይፈልግም (2ኛ ጴጥሮስ 3:9)፡፡ ይህን ስታደርጉ ክብርን ለእርሱ ታመጣላችሁ፡፡

እርሱ በዙሪያችሁ ያሉትን ሰዎች ሕይወት ማስዋብ፣ በእናንተም በኩል ወደ ጽድቅ ሊመራቸው ይፈልጋል፤ ዓላማ ያለው ሕይወት መኖር ማለት ያ ነው ። በሌላ የሕይወታችሁ ዘርፍ ምንም ያህል ፍሬያማና ውጤታማም ብትሆኑ ምንም ዋጋ የለውም፣ በአካባቢያችሁ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ባሉ ክልሎችም ወንጌልን ወደ ጠፉት፣ ተስፋ ቢስ ለሆኑት፣ ለተጎዱት እና ለተጨቆኑት በመውሰድ ነፍሳቸውን ለማሸነፍ ልቃችሁ ለመገኘት መፈለግ

አለባችሁ፡፡

በመልካም ሁኔታ የተኖረ ሕይወት፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ስኬታማ ሕይወት ማለት፣ እግዚአብሔር እንድታደርጓቸው የፈለጋቸውን ነገሮች ስኬታማ ያደረገ ሕይወት ማለት ነው። ስለዚህ ሰዎችን ወደ ጽድቅ በመምራት ውጤታማ በመሆን ክብርን ለእርሱ አምጡ፡፡

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፣ በአለም ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ የወንጌልን ተጽዕኖ ለማሳደር እድል እና ችሎታ ስለሰጠኸኝ አመሰግናለሁ፡፡ ሰዎችን ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ እና ከሰይጣን ኃይል ወደ እግዚአብሔር እየመለስኩ፣ በአንተ ፀጋና እና ጽድቅ አለሜ ላይ ተጽዕኖ እያመጣሁ፣ ዛሬ በክርስቶስ በረከት ሙላት ወደፊት እገሰግሳለሁ፤ በኢየሱስ ስም። አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

የዮሐንስ ወንጌል 15:8; የማቴዎስ ወንጌል 5:16; 2 ቆሮንጦስ 5:15 AMPC

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማርቆስ ወንጌል 6:1-29 & ኦሪት ዘሌዋውያን 24

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 17:1-13 & ኦሪት ዘጸአት 4

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ረቡዕ 24

# ቃሉን በምስል ተመልከቱት

> የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው (2 ቆሮ 4፡18)፡፡

ጥቅሶችን ስታጠኑ፤ በምስል ማጥናትን ተማሩ፤ በመንፈሳዊ አይኖቻችሁ ተመልከቱ፤ እመኑ እናም በዛው መልኩ ተግብሩት፡፡ በህይወታችሁ ሊገለጡ የሚችሉት፣ መንፈሳችሁ ተቀብሎ የያዛቸው በረከቶች ብቻ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቃሉን ስትሰሙም ሆነ ስታጠኑ፤ ድላችሁን፣ ብልፅግናችሁን፣ ጤናችሁን፣ ሰላማችሁን፣ እድገታችሁን፣ ስኬታችሁን ሁሉ በአይነ ህሊናችሁ ከውስጣችሁ ተመልከቱት፣ እናም እንደዚያው አውጁ፡፡

በህይወታችሁ ልታዩ የምትፈልጉት ክብር እና ድሎች በተጨባጭ በእውኑ ዓለም ከመገለጣቸው በፊት፣ በመጀመሪያ በውስጣችሁ ልታዩአቸው ይገባል፡፡ በውስጣችሁ ማየት ከቻላችሁ፤ ከዛ የእናንተ ነው፡፡ በመጀመሪያ በውስጣችሁ የሌላችሁን ነገር በውጪአዊው ልታገኙት አትችሉም፡፡ አንዳንዶች የሳቱት ይህንን ነው፤ እውነት ነው ለማለት በመጀመሪያ በስጋዊ አይናቸው ሊያዩት ይፈልጋሉ፤ ያ እምነት አይደለም፡፡ እምነት ማለት፣ በስጋዊ ስሜቶች ያልታወቁትን ተጨባጭ እውነታ አድርጎ መቀበል ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ በዘፍ 17፡5-6 እግዚአብሄር ለአብርሀም እንዲህ አለው "ከዛሬም ጀምሮ እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፥ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና። እጅግም አበዛሃለሁ፥ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ ነገሥታትም ከአንተ ይወጣል፡፡" አብርሀም በቅድሚያ እራሱን የብዙዎች አባት አድርጎ ሊሚለከት ይገባ ነበር፡፡ እግዚአብሄር በተናገረው ጊዜ አብርሀም ዘጠና ዘጠኝ አመቱ ነበር ሚስቱ ሳራም እንዲሁ ያረጀች እና መካን ነበረች፡፡

ያም ሆኖ ግን መፅሀፍ ቅዱስ በሮሜ 4፡20 እንዲህ ይላል "በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል

አልተጠራጠረም።” በዘፍ 15፡5 ጌታ እንዲህ ብሎ ተናግሮት ነበር “...ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው። ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው”፤ አብርሀምም አመነ፡፡ ከውስጡ የማይቆጠሩትን ተወላጆቹን፤ እንደ ሰማይ ኮከብ የበዙትን ተመለከታቸው፡፡

ዛሬ በህይወታችሁ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው? ልጅ ነውን? መጀመሪያ በውስጣችሁ እዩት፡፡ የቤተክርስትያናችሁን ስፋት ይሆን ወይም አዲስ ስራ፣ አዲስ ንግድ? የዚያን ምስል ፍጠሩ እና በመንፈሳችሁ ውስጥ የራሳችሁ አድርጉት፤ መጀመሪያ በመንፈሳችሁ፤ ምክንያቱም በመንፈሳዊው አለም እውን ሆኗል፡፡ ሀሌሉያ!

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፤ በክርስቶስ እንድጠቀምባቸው ስላዘጋጀህልኝ አስደናቂ በረከቶች ማስተዋልን ስለሰጠኝ ስለዚህ ስጦታህ አመሰግናለሁ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በቃልህ ያገኘሁትን ድሌን፣ ብልፅግናዬን፣ ጤናዬን፣ ሰላሜን፣ እድገቴን እና ስኬቴን በአይነ ህሊናዬ በምስል እመለከተዋለሁ፤ እናም በእምነት አዋጄ ደግሞ ንብረቴ አደርገዋለሁ፡፡ ገመዴ ባማረ ስፍራ ወደቀችልኝ፤ በእርግጥም ርስቴ ተዋበችልኝ፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

መጽሀፈ መክብብ 3:11; ኦሪት ዘፍጥረት 13:14-15; ኦሪት ዘፍጥረት 15:5-6

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 6:30-56 & ኦሪት ዘሌዋውያን 25

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 17:14-21 & ኦሪት ዘጸአት 5

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ሐሙስ 25

## መንፈሱ ፈሷል

> ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ
> (ትንቢተ እዩኤል 2፡28)፡፡

መፅሀፍ ቅዱስ በ1ኛቆሮ 12፡3 ላይ እንዲህ ይላል፡- "...በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር። ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።" በመንፈስ ቅዱስ ካልተሳበ በስተቀር ማንም የጌታ እየሱስን ጌትነት በህይወቱ ሊመሰክር ወይንም እግዚአብሄርን ለማገልገል ሊወስን አይችልም (ሮሜ 10፡8)፡፡ "...በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው።" ቃሉን በልባችሁ የሚያኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ አንድ ሰው በህይወቱ የጌታን ጌትነት ካወጀበት ጊዜ ጀምሮ፣ በእሱ ወይም በእሷ ህይወት ውስጥ አስቀድሞ እየሰራ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

እግዚአብሄር ሰው ሁሉ በወንጌል ለማመን መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስፈልገው በማወቅ በመከፈቻ ጥቅሳችን ላይ ያለውን እንዲህ ብሏል፤ "መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ..." በሥጋ ለባሽ ሁሉ" የሚለውን የተሰመረበትን ሀረግ አስተውሉ፡፡ በተሟላው የአይሁድ መፅሀፍ ቅዱስ ትርጓሜ በበለጠ ይገልፀዋል፡፡ እንዲህ ይላል፡- "ከዚህ በኋላ መንፈሴን በሰው ዘር ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንድ እና ሴት ልጆቻችሁ ትንቢትን ይናገራሉ፡፡" (የተሟላው የአይሁድ መጽሃፍ ቅዱስ 3:1)፡፡ በዚህ በአይሁድ መጽሀፍ ቅዱስ ትርጉም "በሥጋ ለባሽ ሁሉ" የሚለው ትክክለኛ ትርጉም የሰው ዘር በሙሉ ማለት ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ በሰው ዘር ላይ ሁሉ ፈሷል፤ ዛሬ ማንኛውም ሰው ወንጌልን ሰምቶ ሊቀበለው የሚችለው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ በሐዋሪያት መፅሀፍ 2 ላይ ብዙ አይሁዶች ከተለያየ ሀገራት በዓለ ሀምሳን ለማክበር

እንደመጡ ይነግረናል (የሐዋርያት 2፥9-12 አንብቡ)፡፡ ጴጥሮስ ሲያገለግላቸው ሶስት ሺህ የሚያክሉት ክርስቶስን ተቀበሉ፡፡

በቀጣይ ጊዜ ሲያገለግል አምስት ሺህ የሚያክሉ ሰዎች ክርስቶን ተቀበሉ (የሐዋ 4፥4)፡፡ ብዙም ሳይቆይ በእየሩሳሌም በርካታ አማኞች ነበሩ፤ ለምን? በኢዮኤል 2፥28 እንደተገባው የተስፋ ቃል፤ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ሰው ላይ ፈሷል፡፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን፡፡

ወንጌል የምንሰብከውም ለዚህ ነው፤ ምክንያም ሁሉም ሰው የእግዚአብሄርን ቃል ለመቀበል ብቃት አለው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሀጥያት ዓለምን እየፈረደ እና ሰዎችንም ወደ ፅድቅ እየመራ፤ በአለም ዙሪያ እየሰራ ነው፡፡ ጌታ ይክበር፡፡

## ጸሎት

እኔ ከእግዚአብሄር ጋር አለምን በመቀየር አብሮ ሰራተኛ ነኝ፤ ነፍሳትን በማዳንም አብሮ ሰራተኛ ነኝ፡፡ መንፈስ ቅዱስ መንፈሱን ባፈሰሰበት ህዝብ ላይ ወንጌል መስበክ እንዴት ያለ ክብር ነው! ዛሬ በአለም ዙሪያ የሴቶች እና የወንዶች ልብ ወንጌልን ለመቀበል ክፍት ነው እናም በበሁሉም ሀገራት እና ሁሉንም ፍጥረት እያዳረሰ ነው፤ በእየሱስ ስም፡፡ አሜን፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

የማርቆስ ወንጌል 16:15-16; የዮሐንስ ወንጌል 3:16; 1 ቆሮንጦስ 9:16

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማርቆስ ወንጌል 7:1-23 & ኦሪት ዘሌዋውያን 26-27

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 17:22-27 & ኦሪት ዘጸአት 6

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***





# የተባረከ እና የበዛ ሞገስ ያለው

> በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ (ኤፌ 1፥6)።

ከላይ ባለው የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ላይ የተጠቀሰው "የሰጠን" የሚለው ቃል በግሪክ "ቻሪቱ" የሚለው ሲሆን፣ ትርጉሙም ፀጋን መስጠት ማለት ነው፤ ያም ማለት ልዩ የሆነ ክብርን መላበስ፣ ተቀባይነትን ወይም ታላቅ ሞገስን ማግኘት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በትክክል ጥቅሱ ሲነበብ "የበዛ ሞገስ የሰጠን" የሚል መሆን ነበረበት፡፡ ሀሌሉያ!

በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ በተመሳሳይ የተገለጸችው ማርያም ናት፡፡ ሉቃስ 1፥28 እንዲህ ይላል "መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ …አላት።" እናም አሁን እግዚአብሄር እየነገራችሁ ያለውም ይህንኑ ነው፤ ተባርካችኋል፤ የበዛ ሞገስንም አግኝታችኋል፡፡

ማርያም የተባረከች እና ታላቅ ሞገስንም ያገኘች ነበረች፤ ምክንያቱም በእግዚአብሄር ቃል እየሱስን በማህፀኗ ተሸክማ ነበር፡፡ ዛሬ እናንተም በቃሉ ምክንያት በመንፈሳችሁ እየሱስን ተሸክማችሁታል፡፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን፡፡ ቃሉ በእናንተ ውስጥ መኖር ብቻ ሳይሆን፤ ቃሉ ህይወታችሁ ነው፣ ምክንያቱም ከቃሉ ተወልዳችኋልና፡፡ የሰጠን እንዴት ያለውን ህይወት ነው!

ሞገስን ማግኘት ማለት ምን ማለት ነው? ያ ማለት ከመጠን በላይ ተባርካችኋል ማለት ነው፤ ምንም እንኳን የተገባችሁ ሳይመስል እንኳን በእግዚአብሄር ተባርካችኋል፡፡፡ ለዚህ ሞገስ ብቁ ነኝ ወይም አይደለሁም ከሚለው ባሻገር ተመልከቱ፣ እግዚአብሄር ራሱ ብቃታችሁና እና ሙላታችሁ ነው፡፡ 2ኛ ቆሮ 3፥5 ላይ "ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም" የሚለው ለዚህ ነው፡፡

አብዝታችሁ ሞገስን አግኝታችኋል ማለት፤ የምታደርጉት ነገር ሁሉ ይበለፅጋል ማለት ነው፡፡ ሌሎች ሲወድቁ እና ሲያጡ እንኳን እናንተ ምርጥ ትሆናላችሁ፤ ምክንያቱም እናንተ በመንፈስ ቅዱስ ሁሉ ቀርበላችኋል፤ እሱ እያንዳንዱን እርምጃችሁን ያስተካክላል፡፡ ምንም ያክል በነቃፊዎች እና

በተቺዎች ብትከበቡም ምንም ለውጥ አያመጣም፤ እናንተ በፀጋ የተመራችሁ የእግዚአብሄር ወንዶችና እና ሴቶች ልጆች ናችሁ፡፡

የእግዚአብሄር ሞገስ በእናንተ ላይ ስለተገለጠ፤ በሰዎች አእምሮ ለመረዳት የሚያዳግቱ በሮች እና እድሎች ለእናንተ ክፍት ይሆናሉ፡፡ 2ኛ ቆሮንቶስ 9፡8 (የአምሊፋይድ ትርጉም) እንዲህ ይላል "እግዚአብሔር፥ ሁልጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ፥ ጸጋን (ሞገስን እና ምድራዊ በረከትን) ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል።"፡፡ እግዚአብሄር ለእናንተ ያለው መሻት ይህ ነው፡፡ መዝሙር 5፡12 እንዲህ ይላል፤- "አንተ ጻድቁን ትባርከዋለህና፤ አቤቱ፥ እንደ ጋሻ በሞገስ ከለልኸን።" በሁሉም ስፍራ፣ በሁሉም ጊዜ እና አመቱን በሙሉ እንደተባረካችሁ እና የበዛ ሞገስንም እንዳገኛችሁ እወቁ፡፡

## የእምነት አዋጅ

እኔ መለኮታዊ ሞገስ አለኝ፤ ለከበረው ህይወትም ስፍራዬን ይዣለሁ! ፀጋ በቀዳሚው ስፍራ አስቀምጦኛል፤ በጭራሽ ልጎዳ አልችልም! በውበት፣ በክብር እና በማመጣው ተፅእኖ እጨምራለሁ፡፡ ከጌታ ዘንድ የተባረክሁ እንደሆንኩ በሚያውቅ ማንነት እኖራለሁ፤ እመላለሳለሁም፤ እናም በእኔ አማካኝነት በአለሜ ላሉት ሁሉ በረከት ይከፋፈላል፡፡ ሀሌሉያ፡፡

## ለተጨማሪ ጥናት:

2 ቆሮንጦስ 3:5 AMPC; መዝሙረ ዳዊት 1:1-3 AMPC; መዝሙረ ዳዊት 102:13

### የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 7:24-8:1-13 & ኦሪት ዘህልቁ 1-2

### የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 18:1-11 & ኦሪት ዘጸአት 7

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



ቅዳሜ 27

# ወንጌልን የመስበክ ክብር

> ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፥ አስቀድሞ ስለ አንተ እንደ ተነገረው ትንቢት፥ በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ፤ (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥18)።

መቼም ቢሆን እግዚአብሔር ለሰዎች መዳን ወንጌልን እንዲሰብ፡ መላዕክትን ተጠቅሞ አያውቅም። ምንም እንኳን ሃጥያተኛው አትኩሮቱን ወደ እርሱ እንዲያደርግ መላዕክቶችን ቢጠቀምም፣ ለሃጥያተኛው እንዲሰብክ የሚያደርገው ግን፣ ደህንነት የተቀበለን ክርስትያን ነው። ይህም ለቤተ ክርስትያን ወንጌልን የመስበክ ክብር ስለሰጣት ነው። (ሐዋ 10:1-6)

በዚህ ምድር፡ በጨለማ ሃይላት ላይ የመፍረድን ክብር ለእኛ ለቅዱሳን ሰጥቶናል። (መዝሙር 149:5-9) ይህም ምንም ምክንያት ሳንሰጥ ወንጌልን በመስበክ ምድርን በጽድቁ እንሸፍን ዘንድ ነው። የሰይጣን ሃይላት ሁሉ ላይ ስሙን የመጠቀም ሀይል ሰጥቶናል (ማርቆስ 16-17)፡፡ "እንዲህም አላቸው፡- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።... ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ..." ወንጌልን የመስበክ ጉዳይ ደስታችሁ ይሁን። ደግሞም ከመስበክ አትዘግዩ። ምንም እንኳን ማስፈራራት፣ ስደት፣ ተግዳሮት ቢገጥማች፡ ሳትፈሩ ወንጌልን ስበኩ። የእግዚአብሔር ሰራዊት ውስጥ ወታደር መሆናችሁን አትርሱ። ወታደሮች ደግሞ ላመኑበት ነገር ለመቆም የቆረጡ ናቸው።

እውነተኛ ወታደሮች አያፈገፍጉም፤ ደግሞም አይማረኩም። እስከመጨረሻው ይዋጋሉ። ስለዚህ በዚህ መጨረሻ ዘመን የወንጌልን ስራ ለማከናወን ጠንካራና ብርቱ ሁኑ።

ፀልዩ። የኢየሱስ ክርስቶስን ሰማያዊ መንግስት ትወክላላችሁ፤ ለሰዎች ነፍስ ውጊያ ላይ ነን። ነፍሳትን ለማዳን ከመውጣችሁ በፊት፣ ጊዜ ወስዳችሁ የምልጃ ፀሎት አድርጉ። በፀሎት፣ በመንፈሳዊው ዓለም የሰዎችን ነፍሳት አሸንፉ፤ ከዛም የመዳናቸውን ትንቢት ተናገሩ። ከተማችሁ፣ ሃገራችሁና

የዓለም ሃገራት የኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሆናቸውና ነፍሳት በብዛት ለመንግስቱ ስለመማረካቸው ትንቢትን ተናገሩ፤ ።

የሚጸልይ ካህን እና የማስታረቅ አገልጋይ ሚናችሁን ውሰዱ። ቅዱሳን ሁሉ ይህ ክብር እንዳላቸው አስታውሱ። ጌታን አመስግኑት።

## ጸሎት

ውድ አባት ሆይ፥ ለዓለም መስከ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስ በከፍተኛ ፍላጎት፣ የተሰጡና የማይፈሩ ሰራተኞች ያስነሳ ዘንድ፥ እናም የሰዎች ነፍሳት ወንጌልን በደስታ ለመቀበል ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ፡ ወደ መንግስትህም ይፈልሱ ዘንድ እፀልያለሁ።

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 10:13-15; መዝሙረ ዳዊት 149:5-9; ሮሜ 1:16

**የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማርቆስ ወንጌል 8:14-26 & ኦሪት ዘህልቁ 3-4

**የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት**

የማቴዎስ ወንጌል 18:12-20 & ኦሪት ዘጸአት 8

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***



እሁድ 28

# በውስጣችሁ ያለው ክርስቶስ

ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ... (ገላትያ 1፥15-16)፡፡

በመክፈቻ ጥቅሳችን ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን፣ በእሱ ውስጥ ለመግለጥ እንደወደደ ይመሰክራል። ይህ ለሐዋርያው ጳውሎስ ብቻ አይደለም፤ የሁሉ ክርስትያን ጥሪ ነው። የክርስትና ማንነት የሚታወቀው በዕለት ዕለት ኑርዋችሁ ክርስቶስ ሲገለጥና ሲታይ ነው፡፡መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "...ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው" (ቆላስይስ 1:27)፡፡

በእናንተ ውስጥ ክርስቶስን ታያላችሁ? በእናንተ ውስጥና በእናንተ በኩል ሕይወቱ ሲገለጥ ታያላችሁ? ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ከተገለጠ ለሽንፈትና ለድካም ቦታ አይኖራችሁም። ሰውነታችሁ ለበሽታ ቦታ አይኖረውም። ለዘላለም በድል የመኖራችሁ ተስፋ፥ በውስጣችሁ ያለው ክርስቶስ ነው። የማይድን በሽታ ይዝዋችሁ ይሆናል። ክርስቶስ በውስጣችሁ መሆኑን ብታሰላስሉ፣ የዛ በሽታ መጨረሻው ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው።" (ሮሜ 8፥10)፡፡

እጢው ምንም ያህል ትልቅ ቢሆን ግድ አይልም፤ በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ ያጠፋዋል። ጴጥሮስ በየቤቱ እየሄደ ወንድሞችን ይጎበኝ ነበር። በዚያም ከስምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የሚሉትን ሰው አገኘ። በዚያው ሁኔታ እያለ ወንጌልን ተቀበለ። ጴጥሮስ ያለው ነገር ቢኖር "ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈውስሃል፤" ነው (ሐዋ 9:34)፡፡

በሰውነታችሁ ውስጥ የበሽታ ወይም የአካል ጉዳት ምልክት ካለ ክርስቶስ ይፈውሳችኋችል። በውስጣችሁ ክርስቶስ መኖሩን ልብ የምትሉ ሁኑ፤ እርሱ ጥንካሬአችሁ ነው፥ ስለዚህ መራመድ የማትችሉ ከሆነ ተነስታችሁ ተራመዱ። ሁሉን ነገር በእርሱ ውስጥና በእርሱ በኩል ማድረግ ትችላላችሁ! ለዘላለም አሸናፊዎች ናችሁ። እርሱ ነፃ አውጭያችሁ፣ ጥበባችሁ እና ጽድቃችሁ ነው። ጌታ ይባረክ!

## የእምነት አዋጅ

ክርስቶስ ሕይወቴና ሁሉ ነገሬ ነው! የምኖረው፣ የምንቀሳቀሰውና ማንነቴ ያለው በእርሱ ውስጥ ነው ። በእርሱ ለዘላለም አሸናፊ ነኝ፤ ከአሸናፊዎች እበልጣለሁ። ክርስቶስ ነፃ አውጭዬ፣ ጥበቤና ጽድቄ ነው። ስሙ ለዘላለም ይክበር!

## ለተጨማሪ ጥናት:

ሮሜ 8:11; ቆላስያስ 1:26-29 MSG

የአንድ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማርቆስ ወንጌል 8:27-38, 9:1-13 & ኦሪት ዘህልቁ 5-6

የሁለት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

የማቴዎስ ወንጌል 18:21-35 & ኦሪት ዘጸአት 9

**Leave comments on today's devotional at**
***www.rhapsodyofrealities.org***

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# የደህንነት ጸሎት

በዚህ መጻሐፍ እንደተባረካችሁ እናምናለን፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስን በሕይወታችሁ ጌታ እንድታደርጉ እንጋብዛችኋለን።

“ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ኢየሱስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፤ በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡፡ ለእኔ ሲል እንደሞተ እና እግዚአብሔርም ከሞት እንዳስነሳው አምናለሁ፡፡ ዛሬ ሕያው እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወቴ ጌታ እንደሆነ በአፌ አውጃለሁ፡፡ በእርሱ በኩል እና በስሙ ዘላለማዊ ሕይወት አለኝ፡፡ ዳግም ተወልጃለሁ፡፡ ጌታ ሆይ ነብሴን ስላዳንካት አመሰግንሀለሁ! አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡፡ ሀሌሉያ!”

**እንኳን ደስ ያልዎት፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ነዎት።
እንደክርስቲያን በመንፈሳዊ ሕይወትዎ እንዲያድጉ
ከታች በተጻፈው ስልክ ቁጥር ይደውሉ፡፡**


**UNITED KINGDOM:** +44 (0)1708 556 604
+44 (0)08001310604

**NIGERIA:**
+234 1 8888186

**CANADA:**
+1 416-667-9191

**SOUTH AFRICA:**
+27 11 326 0971

**USA:**
+1(800) 620-8522

# ስለ ጸሃፊው

ፓስተር ክሪስ አያኪሎሜ፣ የተነቃቃና ባለብዙ ዘርፍ ዓለማቀፍ አገልግሎት የሚሰጠውን የቢሊቨርስ ላቭ ወርልድ ኩባንያ ፕሬዜዳንት ሲሆኑ፣ ከሰላሳ የሚበልጡ መጽሀፍት እና በአንደኝነት ደረጃ የሚቀመጠውን የእለት እለት የአምልኮ መጽሃፍ የራፕሶዲ ኦፍ ሪያሊቲስ ደራሲ ናቸው፡፡ በመልእክታቸው ወደ በርካታ ልቦች የመለኮታዊ ህይወት እውነታን በማምጣት፣ እጅግ የተሰጡ የእግዚአብሄር ቃል አገልጋይ ናቸው፡፡

የእግዚአብሄርን መለኮታዊ መገኘት ወደ እያንዳንዱ ሰው ቤት የሚያደርሰው፣ “አትሞስፌር ፎር ሚራክልስ” (የተአምራት ከባቢ) የተሰኘው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት ነክቷል፡፡ የላቭ ወርልድ ሳተላይት ቴሌቪዥን መረብን በመጠቀም፣ የእርሳቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለዓለም ሁሉ የክርስቲያን ፕሮግራሞችን ለማዳረስ ችሏል፡፡

በዓለም በታወቀው የሂሊንግ ስኩል (የፈውስ ትምህርት ቤት)፣ የኢየሱስ ክርስቶስን የፈውስ ስራዎች በመግለጥ፣ እና ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ የስጦታ ስራ አማካኝነት ፈውስን እንዲቀበሉ ረድተዋል፡፡

ፓስተር ክሪስ በእግዚአብሄር መገኘት የዓለምን ህዝብ ለመድረስ ያላቸው ፍቅር ጥልቅ ሲሆን፣ በተለያዩ የማዳረስ ዘመቻዎች፣ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራሞች እና በሌሎች በርካታ መድረኮች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በእግዚአብሄር ቃል ድል አድራጊና ዓላማ ያለው ህይወትን እንዲለማመዱ በማድረግ ከሰላሳ ዓመታት በላይ መለኮታዊ ተልእኮአቸውን ተወጥተዋል፡፡

LWPL LoveWorld Publishing

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ

# ማስ ወሻ